# በፍትህ አካላት ባለሙያዎች ሥልጠና ማዕከል

## ለወረዳ ዳኞችና ዐቃብያነ -ህግ የቀድመ ሥራ ሥልጠና
## የተዘጋጀ

## የፍ/ብ/ሥነ- ሥርዓት ህግና ህገ መንግስት
## ሞጁል 2

አዘጋድ ተሻገር ገ/ሥላሴ
የፌ/ጠ/ፍ/ቤት ዳኛ

## ማውጫ

1. መግቢያ

2. የዳኝነት ሥልጣን

   ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን

   የሥረ - ነገር ሥልጣን

   የግዛት ክልል ሥልጣን

3. የፍርድ አፈፃፀም መሠረታዊ ታሳቢዎችና የጋጠሙ ችግሮች

   ከፍርድ በፊት ስለሚሰጡ የዕግድ ትዕዛዞች

   በፍርድ ማስፈፀም ሂደት ንብረት ስለማስከበር

   ስለማይከበሩና በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ስለማይወሰዱ ሀብቶች

   በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርብን አቤቱታ ስለመመርመር

   የሐራጅ ሽያጭ ሥነ - ሥርዓት

4. የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ጉዳዮች በነፃ ስለሚያዩበት ሁኔታና ህገ - መንግስቱ

   ዳኝነት ሳይከፈል ጉዳዮች በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጥ ውሳኔ እና ይግባኝ

   የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍል ክስ ያቀረበው ወገን በረታ ጊዜ ስለሚፈፀም ሥነ ሥርዓት

5. የወጭና ኪሣራ አወሳሰን

   5.1 ማን ይክፈል?

   5.2 ምን ያህል ይክፈል?

## መ ቢሽ

በዚህ ፅሑፍ ለተመለከቱት ሥነ-ሥርአታዊ ድንጋጌዎችም ሆነ በጠቅላላው ስለ ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ምንነት ለመረዳት የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግን ዓላማ ማየቱ አስፈላጊ ነው፡፡

እንደ ሌሎች አገሮች ይኸው ዓላማ ለሌሎችም ሥነ-ሥርዓታዊ ደንቦች መነሻና መንደርደሪያ ሆኖ "የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ደንቦች ገዥ ዓላማ" (The overriding objective of the procedural code) በሚል አይጠቀስ እንጂ ከዳር እስከ ዳር የተካተቱትን ድንጋጌዎች ይዘት እርስ በእርሳቸው አስተሳስረን ስንመለከታቸው ገዥው ዓላማ ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ እና ሥርዓት ባለው መንገድ በመምራት በአጭር ጊዜ እና በአነስተኛ ወጭ እንዲቋጩ ማድረግ ነው፡፡ በሚል ማስቀመጥ ይቻላል፡፡

በተለይም የሥነ - ሥርዓት ድንጋጌዎችን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ እና በክርክሩ አመራር በህጉ በግልፅ ያልተሸፈኑትን ነገር ግን ፍ/ቤቱ በእራሱ በመሰለው እንዲወሰን፣ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በሚያስችል አኳኋን በተደነገገ ጊዜ እንደቅደም ተከተሉ ከትክክለኛው ትርጉም ለመድረስና የተሰጠውንም ሥልጣን (Discretionary power) በአግባቡ ለመጠቀም ይህ የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ዓላማ ቁልፍ ቦታ የያዘ የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡

የፍ/ብሔር ጉዳይ ክርክር አመራር ዝርዝር ሁኔታው በሥነ-ሥርዓታዊ ህግ በዝርዝር ይካተት እንጂ መነሻ ሀሳቡ እና መሠረታዊ መርሁ የአገሪቱ የበላይ ህግ በሆነው ህገ መንግስትና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው የአለም አቀፍ ስምምነቶች ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ መሠረታዊ መብቶችንና ግዴታዎችን ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚያስችል መሣሪያ ሲሆን፣ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገ መንግስት በምዕራፍ ሦስት ለፍ/ብሔር ጉዳይ ክርክር ምክንያት የሆኑት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ተደንግገዋል፡፡ በእያንዳንዱ ዝርዝር ህግ የተካተተውም መብትና ግዴታ እነዚህኑ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው፡፡

እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት መብትን ለማስከበር ሌላውም ግዴታውን እንዲያከብር ለማድረግ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ከተገኘ ለፍርድ ቤት በማቅረብ ፍትህ የማግኘት መብት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 37 "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ወሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው" በሚል የተረጋገጠ ነው፡፡

የፍርድ ስራ አካሄዱም እራሱ እንደዚሁ ህገ - መንግስታዊ ድንጋጌዎችን መሠረት ያደረገ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ከእነዚህም አንዱ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 25 "ሁሉም ሰዎች በህግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በህግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡" በሚል የተደነገገው ህገ-መንግስታዊ መብት በተግባር ሥራ ላይ ከሚውልበት መንገድ አንዱ በፍርድ ቤት ፊት የሚከራከሩ ወገኖች ክርክርን በማቅረብና በማሰማት ረገድ እኩል የመከራከር መብት እንደኖራቸው በማረጋገጥ ነው፡፡

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 9 ላይም "ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ህግ አካል ናቸው፡፡" በሚል የተደነገገ በመሆኑና በተለይም በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሦስት ላይ የተመለከቱትን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን በሚመለከት የተቀመጡት ህገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የዓለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ እንደሚተረጐሙ በአንቀጽ 13 በመልክቷል፡፡

ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ህግጋት አንቀጽ 10 *"ማንም ሰው የተጓደለበትን መብቶችና ግዴታዎች ለማስወሰን ሙሉ <u>የእኩልነት መብቱ ተጠብቆ</u> ነፃ በሆነና አድልዎ በሌለበት ፍ/ቤት ትክክለኛና ይፋ የሆነ ፍርድ የማግኘት መብት አለው"* (ሰረዝ የተጨመረ)፤

እንዲሁም ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነት አንዱ በሆነው የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ዓለም አቀፍ ቃል ኪዳን አንቀጽ 14 *"ሰዎች ሁሉ <u>በፍርድ ቤቶችና በዳኝነት አካላት ፊት በእኩልነት ያታያሉ፡፡</u>"* የቀረበበት የወንጀልም ሆነ የፍ/ብሔር ክስ በሚወሰንበት ጊዜ በህግ በተቋቋመ፣ ሥልጣን ባለው ነፃና ገለልተኛ በሆነ የዳኝነት አካል

ዘንድ የመቅረብና አድልኦ የሌለበትና ግልፅ የሆነ ዳኝነት የማግኘት መብት አለው፡፡ በማለት የተደነገገ በመሆኑ

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 78 (1) “ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ህገ መንግስት ተቋቁሟል፡፡” በማለት እና በአንቀጽ 79(3) “ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፡፡” በማለት ተቋማዊና ሙያዊ የዳኝነት ነፃነቱ በህገ መንግስቱ መረጋገጡና ነፃ የዳኝነት አካል መርህም የፍርድ ስራ አካሄድ ያለአድልዎ በትክክለኛ መንገድ መሠራቱንና የተከራካሪ ወገኖች መብቶች መከበራቸውን ፍ/ቤቶች እንዲያረጋግጡ የሚያስችላቸውና የሚያስገድዳቸው የመሆኑ እውነት ሁሉ በእነዚህ ዓለም አቀፍ ሰነዶችና በህግ መንግስቱ በግልፅ መመልከቱ በህገ መንግስቱም ሆነ በዝርዝር ህገ የመነጨትን መብትና ናዴታዋች ወደ ተግባር ለመለወጥ ሲባል በሚደረገው ሙግት ክሱን ከመሰማት በፊትም ሆነ ክሱ በሚሰማበት ጊዜ እንዲሁም በይግባኝ በሚደረገው ክርክር ሁሉም ወገኖች እኩል መብት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ የመሆኑ ሁኔታ ህገ መንግስታዊ መሠረት ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

በተለይም ፍትህ የማግኘት መብት፣ በፍ/ቤቶች ፊት በእኩል የመታየት የመደመጥ መብት የመሳሰሉትና ከዳኝነት ሥራ አካሄድ ጋር በእጅጉ የተቆራኙት መሠረታዊ መብቶች በህገ መንግስቱ በምዕራፍ 3 ከተካተቱት መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ሥር የሚሸፈኑ በመሆኑ በዚሁ ህገ መንግስት አንቀጽ 13(ለ) “በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግስትና የክልል ህግ አውጭ፣ ህግ አስፈፃሚ እና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበር የማስከበር ኃላፊነት እና ግዴታ አለባቸው፡፡” በማለት የደነገገ በመሆኑና የምንይዘውም የሙያ ኃላፊነት በዜጎች ህይወት በነፃነቶች በመብቶች በግዴታዎችና እና በንብረት ውሳኔ የምንሰጥ እንደመሆኑ መጠን ከላይ የተጣለውን ህገ መንግስታዊ ግዴታ መዘንጋት የሌለብን መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡

እስከአሁን እንዳየነው ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ሊያልቅ የሚባውን ጉዳይ በፍርድ የማስወሰን መብት ያላቸው መሆኑን፣ በፍርድ ቤት አቅርበው በማስወሰኑ ሂደት የመደመጥ መብታቸውን በእኩል ደረጃ በማረጋገጥ ክርክራቸው ያለ አድልዎ በትክክለኛ መንገድ እንዲታይ ማድረግ መሆኑንና በተቻለ መጠን ጉዳያቸውን በአፋጣኝ ተመልክቶ እንዲወሰን የማድረጉ ተግባር ህገ መንግስታዊ መሠረት ያለው መሆኑን በአንድ በኩል

ስንገነዘብ፤ በሌላ በኩል ይህ ህገ መንግስታዊ መሠረት ያለው ሥነ ሥርዓታዊ ህግ በህገ መንግስቱ፣ ህገ መንግስቱን መሠረት ባደረጉት ህጎችና ደንቦች የተቀመጡትን መብትና ግዴታዎች ወደ ተግባር ለመለወጥ የሚቻልበት መሣሪያ መሆኑ ቢታወቅም ለእራሱ ለሥነ ሥርዓታዊ ፍትህ ሲባል የሥነ ሥርዓት ህጉ በሚያዘው መሠረት ክርክሩን የአለመምራት ጉድለት በመሠረታዊ ህጉ የተገኙትን መብቶች እስከማሳጣት ሊደርስ የሚችል የፍትህ መጓደል ውጤት እንደሚያስከትል መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡

## ባ ሥልኃ

በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍ/ቤቶች ብቻ ነው፡፡ በሚል በህገ መንግስቱ አንቀጽ 79(ለ) ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ ይኸው ድንጋጌ ከአንቀጽ 37 ጋር ተገናዝቦ ከታየ ፍ/ቤቶች በማናቸውም ጉዳይ ገደብ የለሽ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይኸውም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን የሚኖራቸው ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚገባው (justiciable matter) ሆኖ ከተገኘ ብቻ ነው፡፡

እንዲሁም በዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በሚል ከተደነገገው "…ወይም ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል …." የሚለው፤

እንዲሁም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 79 (5) በተደነገገው መሠረት ለሃይማኖትና ለባህል ፍ/ቤቶች በህግ የመዳኘት ሥልጣን መስጠቱ፤

እንዲሁም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ቁጥር 4 በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በህግ ካልተገለፀ፤ ክሱን ተቀብሎ ለማከራከር ሥልጣን ያለው ፍ/ቤት ብቻ ነው በሚል መደንገጉ በፍርድ ሊወሰን በሚችለው ጉዳይ ፍ/ቤቶች ብቸኛ ስልጣን የሌላቸው መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ስለሆነም ፍ/ቤቶች አንድን ጉዳይ ተቀብለው ከማየታቸው በፊት በቅድሚያ ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል መሆኑንና አለመሆኑ፤

ጉዳዩ በፍርድ ሊወሰን የሚችል መሆኑ ቢረጋገጥ ይህንን ጉዳይ አይቶ የመወሰኑ ሥልጣን ለሌላ በህግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል ያልተሰጠ መሆኑን በቅድሚያ በእራሳቸው አነሳሽነት ሊመረመሩ ይገባል፡፡

(አባሪ ቁጥር 1 ይመልከቱ)

በህጉ የተቀመጠውን የዳኝነት ሥልጣንም ሆነ በጠቅላላው መርህ የተደገፈውን የሥልጣን ዓይነት መሠረት በማድረግ ያየን እንደሆነ የፍ/ቤቶች ሥልጣን በሦስት ዓይነት ክፍሎች የተመደቡ ናቸው፡፡

1. ብሔራዊ የዳኝነት ሥልጣን
2. በሥረ-ነገር ክርክር ላይ የተመሠረተ የዳኝነት ሥልጣን (የሥረ-ነገር ሥልጣን) እና
3. በግዛት ክልል የተወሰነ የዳኝነት ሥልጣን ናቸው፡፡

አንድ ፍ/ቤት ክስን ተቀብሎ ለማየትና ለመወሰን ሥልጣን አለው የሚባለው እነዚህ ሦስት ሁኔታዎች ተሟልተው የተገኙ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው፡፡

## ብሔራዊ ባ ሥልጎ

ይህ የአንድ አገር ፍ/ቤቶች በአንድ ሰው ወይም ንብረት ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችል ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችላቸው የሥልጣን ዓይነት ነው፡፡ ክስ የቀረበበት ሀገር ብሔራዊ የዳኝነት ስልጣን አለው የሚባለው ከተከሳሹ ወይም የክርክሩ ምክንያት የሆነው ተግባር ከተፈፀመበት ወይም አከራካሪው የሆነው ንብረት ከሚገኝበት ቦታ… ወዘተ ጋር በቂ የሆነ ግንኙነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው፡፡ እነዚህ አያያዡ ሁኔታዎች ናቸው፡፡ ከእነዚህ አያያዥ ሁኔታዎች በአንዱ የተነሣ ፍ/ቤቱ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ በሀገሩ ውስጥ በተቋቋመ የፍርድ አፈፃፀም መዋቅሮች አማካኝነት ወደ ተግባር መለወጡን ለመረጋገጥ የሚያስችለው ሲሆን የሚሰጠውም ፍርድ ከተከሰሰው ሰው መብት አንፃር በዚህ ረገድ ተቀባይነት ያላቸውን መርሆች መሠረት ያደረገ መሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ ፍርዱ በሌሎች አገሮች ዕውቅና አገግኝቶ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ካለው የፍ/ቤቶች አደረጃጀት አንፃር በአዋጅ ቁጥር 25/58 አንቀድ 11(2)(ሐ) የውጭ ሀገርን ፍርድ ወይም ብይን ለማስፈፀም በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች አቤቱታ ማቅረብ እንደሚቻል መደንገጉም ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ ነው፡፡

አንድ ጉዳይ በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች ሊታይ የሚችል መሆኑንና አለመሆኑን ይታያል እንኳ ቢባል ለጉዳዩ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የየትኛው ሃገር ህግ ነው? የሚሉት ጥያቄዎች ከላይ በተመለከቱት አያያዥ ሁኔታዎች ምክንያት የተነሣ እንደሆነ ጉዳዩ በአለም አቀፍ የግል ህግ መሠረት ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ እንደ

ዜግነት ያለው አያያዥ ሁኔታ ባጋጠመ ጊዜ በየትኛው ሃገር ፍ/ቤት ይታያል፣ ተፈፃሚ የሚሆነውስ የየትኛው ሃገር ህግ ነው? በሚለው ረገድ የህግ ግጭቶችን ያስነሳል ይህም ከሆነ ለጉዳዩ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው የአለም አቀፍ የግል ህግ እንጂ የፍ/ቤቱ ሥልጣን ጉዳዩ በያዘው የገንዘብ መጠን ወይም በጉዳዩ ዓይነት መነሻ የሚወሰን አይደለም ወደ ሚለው መደምደሚያ ሁልጊዜ ሊያደርስ የሚችል አይደለም፡፡

**(አባሪ ቁጥር 2 ይመልከቱ)**

## <u>ባሥረ - ር ሥልን (Material Jurisdiction)</u>

ይህ የስልጣን ዓይነት ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት ጉዳዩን በትክክል ተመልክቶ አግባብነት ያለው፤ ፍትህን ያገናዘበ ፍርድ ለመስጠት እንዲረዳ ታስቦ አቅምን ባገናዘበ ሁኔታ የተደረገ የሥልጣን ድልድል ሲሆን፤ ይህንንም በማድረግ እግረመንገዱንም በተለያድ ደረጃ በቅደም ተከተል ለሚገኙ ፍ/ቤቶች የዳኝነት ሥራን ያከፋፈለ ነው፡፡

መሠረቱም ከፍ ያለው ጉዳይ በየደረጃው ከተቋቋሙት ፍ/ቤቶች መከከል ከፍ ባለው ፍ/ቤት እንዲታይ ቢደረግ ፍትሃዊነት ያለው ፍርድ ለማሰጠት ያስችላል ከሚል የተነሣ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ከፍ ያለ፣ ከበድ ያለ ጉዳይ ነው አይደለም? ብሎ ለመለየት የሚያስችል የተሻለ መንገድ እስከሌለ ድረስ ህጉ የለየበት አንዱ መንገድ ጉዳዩ በያዘው የገንዘብ ወይም የንብረት መጠን /ግምት/ ሲሆን፤ ሌላው በገንዘቡ መጠን መለኪያ ሥር የሚወድቅ ቢሆንም ባይሆንም ጉይዩ ውስብስብ የሆነ የህግ ጥያቄ የሚያስነሳ መሆኑን መነሻ በማድረግ የጉዳዩን ዓይነት መሠረት የሚያደርግ ነው፡፡

አንዳንድ ጉዳዮች ሊያስነሱ በሚችሉት የክርክር ባህርይ ምክንያት ለተወሰኑ ፍ/ቤቶች እንዲቀርቡ በህግ ተለይተው ከተመለከቱት በቀር የሥረ-ነገር ሥልጣን የተደለደለው በክሱ በተመለከተው የገንዘብ ወይም የንብረት ግምት መነሻ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 14 እና 15 እንዲሁም የፌደራል ፍ/ቤቶችን ለተቋቋመው በወጣው አዋጅ ቁጥር 25/88 አንቀጽ 8፣11፣14 እና 15 የተደነገገው አስረጅ ነው፡፡

ጉዳዩ የያዘው የገንዘብ መጠን ምን ያህል ነው የሚለው የሚለየውም ከሳሹ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 222 መሠረት ካዘጋጀው የክስ ማመልከቻ ነው። በዚሁ ድንጋጌ መሠረት በተዘጋጀው የክስ ማመልከቻም የሚጠቀሰው የገንዘብ ወይም የንብረት መጠን እንዲሁ በዘፈቀደ ሳይሆን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 226-228 የተመለከቱትን ድንጋጌዎች መሠረት ሊያደርግ ይገባል።

በቁጥር 16 እንደተመለከተው ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን ያለው ሥልጣን በገንዘቡ መጠን ላይ የተመሠረት ከሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 9 ሆነ 231 (1) (ለ) ፍ/ቤቱ ተከሳሹን ከመጥራቱ በፊት የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑና አለመሆኑን ለመወሰን መሠረት የሚያደርገው በማመልከቻው ላይ የተገለፁትን ፍሬ ነገሮች መሠረት በማድረግ በመሆኑ ከሳሹ በተቻለ መጠን እንደ ደንጋጌዎች ሊፈፅም ይገባዋል።

ይህ ሆኖ ካልተገኘ በተከሳሹ በኩል ከሚነሳው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ አንዱ የንብረት ግምት ተጋኗል የሚል በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 250 በተመለከተው መሠረት በአዋቂ፤ በባለሙያ ተገምቶ ከፍ/ቤቱ ሥልጣን በታች ከሆነ በቁጥር 16 እንደተደነገገው የፍ/ቤቱ ሥልጣን በገንዘቡ መጠን የተወሰነ በመሆኑ ክሱ በዚያው ደረጃ ቀሪ ይሆናል። ክስ የሚቀርብበትን ጉዳይ በአግባቡ ገምቶ አለማቅረብ ለሥረ-ነገር ሥልጣን ሲባል ዋናው ክርክር ከመሰማቱ በፊት ሆነ ከፍርድ በፊት ባለው በማናቸውም ደረጃ ክስን ቀሪ ሊያደርግ የሚችል ከመሆኑም በላይ የተሰጠን ፍርድ በይግባኝ ለመሻር የሚያበቃ ይሆናል። እንዲሁም በዚህ ፅሑፍ የመጨረሻ ክፍል በወጪና ኪሣራ ጉዳይ ወደ ፊት እንደምናየው በዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ምክንያት ላልተገባ ወጭ የሚዳርግ ይሆናል።

የሥረ-ነገር ሥልጣን የሚወሰነው በገንዘቡ መጠን እዳ በጉዳዩ ዓይነት ቢሆንም የፌዴራል መንግስትን አደረጃጀት ተከትሎ የጉዳዩ ባለቤት ማን ነው? የሚለውንም ይከተላል።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግስትና በክልሎች የተዋቀረ ነው የሚለውን መነሻ በማድረግ የዳኝነቱም ሥልጣን በፌዴራል መንግስቱ እና በክልል መንግስታት መካከል እንደተከፋፈለ በህገ መንግስቱ አንቀጽ 50 እና 51 ሥር

ተደንግጓል። በዚህም መሠረት በአንቀጽ 80 *"የፍ/ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን"* በሚል ርዕስ በፌዴራል ጉዳዩች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣኑ በፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት፤ በክልል ጉዳዮች ላይ በክልሉ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሥልጣኑ እንዳረፈ ተመልክቷል። በመሆኑም የክልል ፍ/ቤቶች በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን መሠረት ካልሆነ በቀር የፌዴራልን ጉዳይ ለማየት፤ እንዲሁም የፌዴራል ፍ/ቤቶች የክልልን ጉዳይ ለማስተናገድ የሚያስችል ሥልጣን የላቸውም።

አንድ ጉዳይ የፌዴራል ነው መልስ የክልል የሚለውን ለመለየትም መነሻ የሆነው አዋጅ ቁጥር 25/88 ሲሆን፤ በዚሁ ህግ አንቀጽ 5 ሥር በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ብቸኛ ሥልጣን ያላቸው የፌዴራል ፍ/ቤቶች ናቸው። በእነዚህ ጉዳዮች ላይ የክልል ፍ/ቤቶች ከላይ እንደተመለከተው በህገ-መንግስቱ በተሰጣቸው የውክልና ሥልጣን ካልሆነ በቀር የማየት ሥልጣን አይኖራቸውም።

በዚህ አኳኋን በጉዳዩ ባለቤትነት የተደረገው የሥልጣን ክፍፍል እንደተጠበቀ ሆኖ ከጉዳዩ አካሄድ ቅደም ተከተል አንፃር በህግ የተሰጠውን መብት ለማስከበር ክስ ለማቅረብ የፈለገ ወገን በማን ላይ ክስ እንደሚያቀርብ ከወሰነ በኋላ ክሱን በየትኛው ደረጃ ለሚገኝ ፍ/ቤት ማቅረብ እንዳለበት መለየት ይኖርበታል። ክሱም መቅረብ ያለበት ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን የሥረ-ነገር ሥልጣን ላለው ፍ/ቤት ነው።

ይህ የሥልጣን ዓይነት ታሳቢ የሚያደርገው የፍ/ቤቱን ዓቅም /ችሎታ (Competence of the court) በመሆኑ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ተከሳሹን ከመጥራቱ በፊት ከሚያጤናቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ በመሆኑ ይኸው የሥልጣን ዓይነት ያለው መሆኑንና አለመሆኑን በቅድሚያ መለየት ያለበት ስለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 9፣ 231 ተመልክቷል። ክርክርን በመምራት ረገድ ይህ በፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት የሚከናወን ተግባር ነው። ይህ ሥርዓት ከታለፈ ወይም በፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ሳይመረመር የቀረ/የታለፈ ከሆነ በፍ/ብሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244 (2) (ሀ)መሠረት በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት በተከሳሽ አማካኝነት ክርክሩ መቅረብ አለበት። ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮ የሥረ-ነገር ሥልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለይቶ በዚሁ ህግ በቁጥር 245 መሠረት ብይን ይሰጣል። እንደ ሥነ-ሥርዓት ህጉ ዓላማ ክርክርን በአፋጣኝ ፣ በአነስተኛ ወጭ ለመቋጨት ሲባል፡ የሥረ-ነገር ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ክስ መቅረቡ፡

ከተረጋገጠ ዋናው ክርክር ከመስማቱ በፊት ባለው፡ የክርክር ደረጃ (at the per-tricot stage) ጉዳዩ ዕልባት ሊያገኝ እንደሚችል የሚያስገነዝብ ሥርዓት መሆኑን ያስገነዝባል፡፡

ይሁን እንጂ ጉዳዩን በትክክል ተመልክቶ መወሰን ሌላው የሥነ ሥርዓት ህግ ዓላማ መሆኑም የሚዘነጋ አይደለም፡፡ ስለሆነም የሥረ-ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን ክሱ እንደቀረበለት ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት መለየት ካልቻለ፤ ተከሳሹም በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ነጥብነቱ አንስቶ ካልተከራከረበት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(3) እንደተመለከተው ዓቅም የሌለው ፍ/ቤት ፍትህን ያገናዘበ ውሳኔ ይሳጣል ተብሎ ስለማይገመትና በዚህም የተነሣ የሥረ-ነገር ሥልጣን አለመኖር ትክክለኛውን ፍርድ ለመስጠት የሚያሰናክል ሆኖ ስለሚገኝ በመቃወሚያ ማቅረቢያ ጊዜ ባይቀርብም እንደተተወ ከማይቆጠሩትና ከፍርድ በፊት በማናቸውም ጊዜ ሊቀርቡ ከሚችሉት የመቃወሚያ ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ ስለሆነም ከፍርድ በፊት ክርክሩ በየትኛውም ደረጃ ቢገኝ ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነትም ሆነ በተከራካሪው ወገን ጠያቂነት የሥረ-ነገር ሥልጣን የሌለው መሆኑን አንደተረዳ መዝገቡን መዝጋት ይኖርበታል፡፡

በዚህ አኳኋን ሳይታረም ሙሉ ክርክር ተደርጎ ማስረጃ ተሰምቶ የተወሰነ መሆኑ፤ እንዲሁም የይግባኝ መብቱ እስኪፈቀድ ድርስ በየደረጃው ታይቶ ውሳኔ ያረፈበት መሆኑ ቢታወቅም፤ የሥረ-ነገር ሥልጣን ጉዳይ ሊጣስ የማይገባው የመርህ ጥያቄ እንደመሆኑ መጠን፡ በየደረጃው በነበረው ክርክር የታየው ወጭ የባከነው ጊዜና ድካም ግምት ውስጥ ሳይገባ በመጨረሻው በሰበር ደረጃም ቢሆን ሊሻር የሚችል መሆኑ ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ ነው፡፡

(አባሪ ቁጥር 3)

**<u>በ ዘብ ባማቭ መቱ ሴሎ ቤቱ ም</u>**

በጉዳዩ የተካተተው የገንዘብ መጠን አነስተኛ ቢሆንም ሊያስነሳ የሚችለው የህግ ጥያቄ የተወሳሰበ ከሆነ ከፍ ባለው ፍ/ቤት የሚታይ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ሌሎች በገንዘቡ የማይገመቱ አቤቱታዎች ለመጀመሪያው ደረጃ (በክልል ለወረዳ ፍ/ቤት) መቅረብ ያለባቸው መሆኑ በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 18 ሥር ተመልክቷል፡፡

ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ ጉዳዩ በገንዘብ ሊገመት የሚችል መሆኑ እየታወቀ እና በያዘው የገንዘብ መጠን መሠረት ክሱ ከፍ ባለው ፍ/ቤት መቅረብ ሲገባው የክሱን

አርዕስት በማየት ብቻ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 18 መሠረት የቀረበ ክስ በሚል የሥረ- ነገር ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ክስ ሲቀርብ ይስተዋላል።

ይህም ዓይነት  የክስ አቀራረብ ባለማወቅ ሊፈፀም የሚችል መሆኑ እንዳለ ሆኖ ስለ ክሱ አቀራረቡ በቂ እውቀት እያለ ሆን ተብሎ ፍ/ቤቶችን ለሚሰጡት አገልግሎት በተመላሽ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ላለመክፈል ሲባልና ሥልጣን በሌላቸው ፍ/ቤት ክስን በማቅረብ ያለአግባብ የፍርድ ባለመብት ለመሆን ከመሻት የሚመነጭ ተግባር ሆኖ የሚታይበት አጋጣሚ ይከሰታል።

ለአብነት ለመጥቀስ ያህል የክሱ መነሻ ውል ሆኖ የውለታውም ጉዳይ በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1675 እንደተመለከተው በገንዘብ፣ በንብረት ወይም በማናቸውም ገንዘብ ነክ የሆነን ጉዳይ የሚመለከት ሆኖ ከዚሁ ጋር በተያያዘ ውል ይፍረስልኝ፤ ወይም እንዲውሉ ይፈፀምልኝ/ ይርሰረዝልኝ/ የሚል ክስ የሚቀርብ ከሆነ በውሉ በተካተተው የሀብት ግምትና በዚሁ ምክንያት ሊደርስበት የሚችለውን ጉዳት ወይም ሊያገኝ የሚችለውን ጥቅም በገንዘብ አስልቶ ክስ ማቅረብ ሲገባ በደፈናው ውል "ይፍረስልኝ" በገንዘብ ሊገመት የማይቻል አቤቱታ እንደሆነ በማስመሰል የሥረ -ነገር ሥልጣን ለሌለው ፍ/ቤት ማቅረብ፤

ሌላው የክሱ ርዕስ፤ "ሁከት ይወገድልኝ" በሚል ይጠቀስና ይህም ክስ በገንዘብ አይገመትም ስለሆነም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 18 መሠረት በወረዳው ፍ/ቤት ሊታይ ይገባዋል በሚል የሚቀርበው የክስ አቀራረብ ነው። ሆኖም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1149 (1) መሠረት የተወሰደን ነገር ለማስመለስ የሆነ እንደሆነ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 226 (3) መሠረት ክስ የሚቀርብበት ጉዳይ በገንዘብ ተተምኖ ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ ።

ሁከት ይወገድልኝ ስለተባለ ብቻ ክስ የሚቀርብበትን ፍ/ቤት ሥልጣን ሊወሰን የሚችል አይሆንም

**(አባሪ ቁጥር 4 ይመልከቱ)**

ሥልጣን ሲባልም በመጀመሪያ ደረጃ የሚቀርብን ክስ ብቻ ሳይሆን በይግባኝም ሆነ በሰበር የማየትንም ሥልጣን የሚጨምር በመሆኑ ከዚሁ ጋር በተያያዘ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትን በሰበር ችሎት የማረም ሥልጣን ወሰን እንመለከታለን።

## የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን

የኢትዮጵያ የሰበር አወቃቀር ጣምራ የፍ/ቤቶች ሥርዓት የያዘውን የፌዴራል መንግሥትን አደረጃጀት ተከትሎ የተዘረጋ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ሁለት ዓይነት የሰበር ሥርዓት ተቀምጧል፡፡

ከዚህም በመነሳት በክልል ጉዳዩ የክልል ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ተመልክቶ የሰጠውንም ውሣኔ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር አይቶ የማረሙ ሥልጣን ህጋዊ መሠረት ያለው ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ለዚህም ጥያቄ ምክንያት የሆነው የሰበር ስልጣን ሰጪው ድንጋጌ ለትርጉም በር በሚከፍት አኳኋን በመቅረፁ ይመስላል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በፌዴራል ጉዳይ ላይ ብቻ የተገደበ ሊሆን ይገባል የሚለው አንደኛው የክርክር መስመር ሲሆን ሌላው ደግሞ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤቶች በክልል ጉዳይ በሰበር ተመልክተው የሰጧቸውና የመጨረሻ ፍርድ ይጠቃለላል የሚለው ነው፡፡

የመጀመሪያው የክርክር መስመር በህገ-መንግሥቱ የተቀመጠውን ፌዴራላዊ የመንግሥትን አወቃቀር ምርኩዝ የሚያደርግ ነው ይኸውም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልል መንግስታት የተዋቀረ ነው ክልሎች የየራሳቸው የህግ አውጪነት የህግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አሏቸው፡፡ ለፌዴራል መንግሥቱ የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር እንዳለበት ለክልሎች የተሰጠውን ሥልጣን በፌዴራል መንግሥቱ መከበር አለበት በማለት ህገ-መንግሥቱ የሥልጣን ወሰን አበጅቷል፡፡ የፍ/ቤቶች ጣምራነት ሥልጣን በማለው አንቀጽ 80 (2)

ላይ የክልል ጠ/ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል ተብሎ የተደነገገውም ይህንን አወቃቀር ተከትሎ ነው፡፡

ስለሆነም በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) "….መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ማናቸውም የመጨረሻ ውሣኔ …" የሚለው ሐረግ በጥቅል ደረጃ ለትርጉም በር በሚከፍት ሁኔታ የተቀመጠ ቢሆንም የመንግሥትን አወቃቀር በሚመለከተው ከተቀመጡት ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ አንፃር ታይቶ መሠረታዊ የህግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የፌዴራል ጉዳይ የመጨረሻ ውሣኔ በሚል ሊተርጎም ይገባዋል፡፡ የክልልንም ጉዳይ እንደሚጨምር ተደርጐ ከተወሰደ ግን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤትን የሰበር ሥልጣን የሰበር ሰበር ያስመስለዋል፡፡ ይህ ደግሞ ምክንያታዊ አይሆንም የሚለውን ነጥብ በማንሳት ነው፡፡

ከዚህ ተቃራኒ የሆነው ደግሞ በህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80 (3) (ሀ) " … ማናቸውንም የመጨረሻ ውሣኔ…" የሚለው ሐረግ ግልጽና የማያሻማ ነው በህግ አተረጓጐም መርህ መሠረት ህግ ግልጽ ሆኖ ከተገኘ የትርጉም ሥራ የማያስፈልገው በመሆኑ እንዳለ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ይኸው አገላለጽ አሻሚ ነው ትርጉም ያስፈልገዋል እንኳ ቢባል አግባብነት ያላቸውን ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸው አስተሳስረን በማየት ልንተረጉመው ይገባል፡፡ በአንቀጽ 80 (2) "የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል" ብሎ ከደነገገ በኋላ በንዑስ አንቀጽ 3 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው ቢኖርም በማለት መደንገጉ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር አይቶ የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸውንም ጉዳዮች ቢሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ለማረም ሥልጣን ያለው መሆኑን የሚያስገነዝብ በመሆኑ፤

ምናልባትም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ሲኖርም የሚለው የአንቀጽ 80 (3) አነጋገር የጉዳዩ ባለቤት ማን ነው የሚለውን የሚከተል መሆኑን ስለሚያስረዳ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት በፌዴራል ጉዳይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ቢኖረውም በዚሁ ፍ/ቤት የተሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ በጠቅላይ ፍ/ቤቱ ሰበር ሰሚው ችሎት ሊታይ የሚችል መሆኑን፤ በተመሳሳይ የክልል ጠ/ፍ/ቤት በክልል ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ቢኖረውም መሠረታዊ የህግ ስህተት ከተገኘ

በክልሉ ጠ/ፍ/ቤት ሰበር ሰሚው ችሎት እንደገና ሊታይ የሚችል መሆኑን ለማመልከት በቅደም ተከተል የተቀመጠ አቀራረጽ ነው የሚል ትርጉም ሊነሳ ይችላል።

ሆኖም ከላይ ከተመለከቱት ሁለት አይነት የህግ አተረጓጐም ዘዴዎች በተጨማሪ ህጉ አሻሚ ነው ከተባለ የህግ አውጪውን ሀሳብ መሠረት በማድረግ ሊተረጐም ይገባዋል። የህግ አውጪው ሀሣብ ምን ነበር የሚለውንም የህገ-መንግሥቱ ጉባኤ ከያዛቸው ቃለ ጉባኤ (Minutes) መረዳት ይቻላል።

የፍርድ ቤቶችን አወቃቀርና አደረጃጀት በተመለከተ የተዋቀረው ኮሚቴ ያዘጋጀው ንዑስ አንቀጽ የሰበር ሥልጣንን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ብቻ እንጂ ለክልል ጠ/ፍ/ቤቶች እንዳልሰጠና በኋላ ግን የሰበር ሥልጣን ለክልሎችም እንደሚያስፈልጋቸው በማየት እንደአስፋፋው ከቁጥር 26-29 ገጽ 34-36 ያለው ቃለ ጉባኤ ስለሚያስረዳና ክርክሮችንም በፍትሐዊነት መቋጨት ያስችላል።

በአገሪቱ ወጥ የሆነ የህግ አተረጓጐም እንዲኖር ይረዳል የሚሉትን ነጥቦች መነሻ በማድረግ ምንም እንኳ የክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት በሰበር ሥልጣኑ ተመልክቶ እንደገና ያየው ቢሆንም የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር በፌዴራል ጉዳይ ላይ ብቻ ሳይሆን የክልልንም ጉዳይ በሰበር የማረም ሥልጣን ይኖረዋል በማለት በዚሁ ሰነድ ገጽ 43 ያስቀመጠ በመሆኑ፣ ህገ-መንግሥቱ አንቀጽ 80 አቀራረጽ ከላይ ለተነሳው ክርክር በር ከፍቷል ከሚባል በቀር የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰበር ሥልጣን በፌዴራል ጉዳይ ሳይወሰን የክልል ፍ/ቤቶች የሰጧቸውንም የመጨረሻ ውሣኔዎች በሰበር የማረም ሥልጣን ህገ-መንግሥታዊ መሠረት ያለው መሆኑን ያስረዳል የሚለው ነው።

**ባ ዛ ክልል ሥልጎ (Local Jurisdiction)**

ይህ ዓይነቱ የዳኝነት ሥልጣን አንድን ጉዳይ ተቀብሎ ለመስማት እና ለመወሰን ዐቅም ካላቸው ፍ/ቤቶች መካከል በየትኛው ፍ/ቤት ቀርቦ መታየት እንዳለበት የሚያመለክት ነው፡፡ ያስፈለገበትም ምክንያት ለተከራካሪ ወገኖች ይልቁንም ለተከሳሹና ለምስክሮቹ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ሲባል ነው፡፡

ክስ የቀረበለት ፍ/ቤትም ክሱን ተቀብሎ ለማከርከርና ለመወሰን በህጉ መሠረት በግዛት ክልል ላይ የተመሠረተ የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑን ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 19 እስከ 30 ድረስ የተመለከቱትን ድንጋጌዎች በመከተል ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡

አንድ ፍ/ቤት በግዛት ክልል ላይ የተመሠረተ የዳኝነት ሥልጣን ያለው መሆኑንና አለመሆኑን ለመለየት መሠረቱ በዚሁ ህግ በቁጥር 19 ላይ ተደንግጓል፡፡

በዚህም ድንጋጌ መሠረት የግዛት ክልል የዳኝነት ሥልጣን አስመልክቶ የተነገሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ወይም በተለዩ ሁኔታ እንዲወሰን በሌላ ህግ ካልተገለፀ በቀር በህጉ መሠረት ማናቸውም ክስ መቅረብ የሚገባው ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሠራበት ክፍል በሚያስችለው ፍ/ቤት እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ይህም ማለት በቁጥር 19 በተመለከተው ብቻ ሳይሆን በተለየ ቦታ መቅረብ እንዳለበት አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ በልዩ ድንጋጌ ወይም ፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተደነገገ (ቁጥር 25) ክሱ ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሠራበት ክፍል ሊቀርብ እንደማይችል የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 20 እና ተከታዩቹ ክሱ ተከሳሹ ከሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ ከሚሰራበት ቦታ ውጭ በሌላ ቦታ ክስ ማቅረብ እንደሚቻል ፈቃጅ በሆነ ሁኔታ ተደንግጎ ከተገኘ (ቁጥር 24(1) እና 27) ክሱ በከሳሹ ምርጫ ከሁለት በአንዱ ክስ የመመስረት መብት ያለው መሆኑን አመልካች ነው፡፡ ምክንያቱም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ

19 ላይ ከዚህ ቀጥሎ ባሉት ቁጥሮች የተነገረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሚለው ሀረግ ከቁጥር 19 ጀምሮ ያሉትን ፈቃጅ ድንጋጌዎች ሥልጣን ሊያስቀር የሚችል መነሻ አባባል ባለመሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም የግዛት ክልል ሥልጣን ተከሳሹ በሚኖርበት ወይም ለግል ጥቅሙ በሚሠራበት ቦታ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን እንደሌሎች ተከታይ ድንጋጌዎች ይዞት የሚወሰን ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 10(1) ‹‹… ከቁጥር 19 እስከ 30 በተነገረው መሠረት ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት ነገሩን ለመቀበል የሚችል የግዛት ክልል ሥልጣን ያለው ሌላ ፍ/ቤት መኖሩን ምክንያት በማድረግ ብቻ የቀረበለትን ክስ አልቀበልም ለማለት አይችልም በማለት የተደነገገውም ይህንኑ የቁጥር 19 ድንጋጌን ተርጉሞ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ ከአንድ ፍ/ቤት በላይ ሊቀርብ የሚችልበት ሁኔታ የሚያመክት ነው፡፡

ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የግዛት ክልል ሥልጣን የሌለው መሆኑን እንደተረዳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 231(1) (ለ) መሠረት ተከሳሹን ከመጥራቱ በፊት ሥልጣን የሌለው መሆኑን በመግለፅ መዝገቡን ዘግቶ ማሰናበት ይገባዋል፡፡ ይህም ደረጃ ከታለፈ በግዛት ክልል ሥልጣን አወሳሰን ተጠቃሚው ተከሳሹ እንደመሆኑ መጠን እንደተከሰሰ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 244(2)(ሀ) መሠረት መቃወሚያ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ይህ መቃወሚያ መቅረብ በሚገባው ጊዜ ካልቀረበ የግዛት ክልል ሥልጣን አለመኖር ትክክለኛ ፍርድን ለመስጠት የሚያሰናክል ባለመሆኑ ተከሳሹ እንደተወው ከሚቆጠሩት የመቃወሚያ ምክንያት አንዱ በመሆኑ ዘግይቶ የሚያቀርበው ክርክር ተቀባይነት አይኖረውም፡፡

መቅረብ በሚገባው ጊዜ መቃወሚያው ቀርቦ እንኳ ፍ/ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 245 መሠረት ህጉን በተሳሳተ መንገድ ተርጉሞ ሥልጣን አለኝ ብሎ ክርክሩን ቢቀጥል እና በመጨረሻም በዋናው ነገር ላይ ውሳኔ ከሰጠ የግዛት ክልል ሥልጣን በሌለው ፍ/ቤት በመታየቱ የተነሣ ፍትህ የተጓደለበት መሆኑን ተከሳሹ ካላረጋገጠ በቀር የግዛት ክልል ሥልጣን በሌለው ፍ/ቤት ታይቶ የተሰጠ ውሳኔ መሆኑን ብቻ መሠረት በማድረግ የይግባኝ አቤቱታ ማቅረብ እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 10 ተመልክቷል፡፡

## (አባሪ ቁጥር 5)

### ባምርታ ወኻኸም መሠረ ዊ ሳቢዎ ቨ ኀሙ ሮ

አፈፃፀም ፍርድ ቤት የሰጠውን ፍርድ በእራሱ አማካኝነት ወደ ተግባር የሚለውጥበት ሥርዓት ነው፡፡ ስለፍርድ አፈፃፀም የተደነገጉትን ድንጋጌዎች በመከተል ፍርድን በተግባር መተርጎም እንደመሆኑ መጠን የማስፈፀሚያ ሥርዓቱ በጥቅሉ የፍ/ብ/ሥ/ሥ ህጉን መሠረታዊ ዓላማ ተከትሎ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲፈፀም በሚያስችል አኳኋን የተዋቀረ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተግባር እንደሚታየው ክስ አቅርቦ ለማስፈረድ ከሚወሰደው ውጭ ጊዜና ጉልበት ባልተናነሰ ሁኔታ የተፈረደን ፍርድ ለማስፈፀም የሚጠይቀው ወጭና ጊዜ በልጦ የሚታይበት ጊዜ ይከሰታል፡፡ ምክንያቶቹ በርካታ ናቸው፡፡

ከነዚህም ጥቂቶቹ፡-

- በተፈረደው ፍርድ ላይ የይግባኝ አቤቱታ በመቅረቡ ምክንያት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 332-335 መሠረት በሚሰጠው የማገጃ ትዕዛዝ፤
- ፍርድ በማስፈፀም ሂደት ከርህራሄነት የተነሣ ህጉ የሚያዘውን በጥብቅ ከመከተል ይልቅ በእራስ ህሊና የመመራቱ አዝማሚያ መታየቱ፤
- በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 445-447 መሠረት በሽያጭ አፈፃፀም ጊዜ የሥነ ሥርዓት ጉደለት አለ በሚል ሳቢያ የሚነሳው ክርክር
- በተከበረ ወይም በተያዘ ንብረት ላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ባለይዞታ ነኝ ባይ የሚያቀርበው አቤቱታ፤
- ገኘው የገዛበትን ገንዘብ በህግ በተወሰነው ጊዜ አለመክፈል … ወዘተ የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ፍርድን በማስፈፀም በኩል ለሚከሰተው መጓተት ዓበይት የሆኑትን ምክንያቶች በሦስት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

ይኸውም፡-

1. ህጉ በሚያዘው መሠረት ያለመመራት፣ በህጉ እና በልምድ መካከል ያለው ልዩነት፣
2. ድንጋጌው በእራሱ ግልፅ ያለመሆን ወይም ሁሉን ሁኔታ ያለመሸፈን፣
3. ረቂቁ ከተዘጋጀበት ቋንቋ ወደ አማርኛ ሲተረጎም የተፈጠረው የትርጉም ስህተት (ክፍተት) በዋነኛነት ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡

ከላይ የተመለከቱት ዓበይት ችግሮች ከማታይባቸው ድንጋጌዎች ጥቂቶቹን ለመመልከት ያህል፡-

**<u>በህ ፡ ቨስመመሬ ሁ ፣</u>**

የፍርድ ባለመብት ፍርድ እንዲፈፀምለት በቁጥር 378 መሠረት ማመልከቻ ሲያቀርብ አፈፃፀሙን የያዘው ፍርድ ቤት በቁጥር 386 መሠረት እንደፍርዱ የማይፈፅምበት ምክንያት ካለው ያስረዳ ዘንድ የማመልከቻው ግልባጭ ከመጥሪያ ጋር ይላክለታል፡፡

በቀነ ቀጠሮውም በቀረበ ጊዜ ፍርድ ቤቱና የፍርድ ባለገንዘቡ ለሚያቀርቡለት ጥያቄ በመሃላ ቃል የተደገፈ መልስ ይሰጣል፡፡ በማለት በቁጥር 386(1) እና (2) ተደንግጓል፡፡ በዚህ አኳኋን መፈፀም ሲገባው የፍርድ ባለዕዳው ለቀረበበት የአፈፃፀም ክስ መልሱን ይዞ እንዲቀርብ፤ ይዞ በቀረበ ጊዜም የፍርድ ባለመብቱ የመልስ መልሱን እንዲያቀርብ ተከታታይ ቀጠሮ የመስጠቱ አሠራር በህግ ያልተደገፈ እና አላስፈላጊ ተግባር ነው፡፡ በአፈፃፀም ምክንያት የሚነሳው ክርክር አጭርና ግልፅ ነው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 375፣396፣397፣398 መሠረት ዕዳውን ከፍሎ ከሆነ፣ የፍርድ ባለዕዳነቱን ግዴታ ፈፅሞ ከሆነ፣ የመቻቻል ጥያቄ ካለው ይህንኑ ለማረጋገጥ እና ፍርዱ የሚፈፀምበትን መንገድ የሚያሳይ ከሆነ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ሌላ የፅሑፍ ክርክርን የሚጋብዝበት ሁኔታ አይታይም፡፡ ይህም ከላይ ከፍ ሲል እንደተገለፀው የፍርድ ባለዕዳው በአካል በተገኘበት ጊዜ በመሃላ ሥር ሆኖ የሚያረጋግጠው ተግባር ነው፡፡

በዚህ አኳኋን ፍርዱ እንዳይፈፀም የሚቃወምበትን ምክንያት ቀርቦ ካላስረዳ ወይንም ያልቀረበ እንደሆነ በቁጥር 386(3) እና 392(1) መሠረት ፍ/ቤቱ ውሳኔው እንዲፈፀም ወዲያውኑ ትዕዛዝ መስጠት አለበት፡፡

የፍርድ ባለዕዳው በመጥሪያው መሠረት ሳይቀርብ የቀረ እንደሆነ ታስሮ እንዲቀርብና ለሚደረግለት ጥያቄ ወይም ምርመራ መልስ እንዲስጥ የሚታዘዘው ገንዘብ እንዲከፍል የተፈረደን ፍርድ ለማስፈፀም እንደሆነ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 3 እና 4 መገንዘብ ይቻላል፡፡

እንደዚሁም የፍርድ ባለዕዳው ፍርዱ እንዲፈፀም መሰናክል በመፍጠር ወይም የፍርዱን አፈፃፀም ለማዘግየት ንብረቱን ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ክልል ውጭ ለማሸሽ ወይም ራሱ ከፍርድ ቤቱ ሥልጣን ክልል ውጭ ለመውጣት፣ ለመሸሽና ለመሰወር ያቀደ መሆኑን የሚያረጋግጥ በቃለ መሃላ የተደገፈ ማመልከቻ የቀረበለት እንደሆነ በቁጥር 386(1) መሠረት መጥሪያ ማስተላለፍ ሳያስፈልግ በቀጥታ ታስሮ እንዲቀርብ እና እንደፍርዱ የማይፈፀምበትን ምክንያት እንዲያስረዳ ፍ/ቤቱ ማዘዝ እንደሚችልም በቁጥር 387 ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም በመጀመሪያው ቀነ ቀጠሮ በዚህ አኳኋን እንደ ህጉ አነጋገር የአፈፃፀም ሥርዓቱ ከተከናወነ አፈፃፀምን ሳይንዛዛ መምራት እና በአጭር ጊዜ ለመቋጨት ያስችላል፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ከተዘረዘሩት ድንጋጌዎች መካከል ግልፅ ያልሆነ ወይም ሁሉን ሁኔታዎች የማይሸፍኑ ወይም በትርጉም ስራ ምክንያት በተፈጠረው ክፍተት ለጉዳዩ መጓተት ምክንያት የሆኑትን ድንጋጌዎች ለአብነት ለመጥቀስ ያህል፡-

ፍርዱን እንዲያስፈፅም የታዘዘ ፍ/ቤት ስላለው ሥልጣን በሚደነግገው በቁጥር 347(1)"…ስለፍርድ አፈፃፀም የሚሰጠው ትዕዛዝና በትዕዛዙም ላይ ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ሥልጣን ዋናውን ፍርድ ከወሰነው ፍርድ ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር እኩል ሆኖ ይቆጠራል፡፡" በማለት በመደንገጉ አፈፃፀሙን በሚመለከት የይግባኝ አቤቱታ ለየትኛው ፍ/ቤት ይቀርባል? ለሚለው ጥያቄ አሳሳች ምላሽ የሚሰጥ ድንጋጌ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

ፍርዱን የሰጠው የከፍተኛው ፍርድ ቤት ቢሆንና ፍርዱን እንዲያስፈፅም የተወከለው ደግሞ የወረዳው ፍ/ቤት ቢሆን ከወረዳው ፍ/ቤት ይግባኝ ስለሚባልበት ሁኔታ ያለው ሥልጣን ከከፍተኛው ፍ/ቤት ሥልጣን ጋር እኩል ሆኖ ይቆጠራል በማለት በቁጥር 374(1) የተቀመጠ ስለሆነ በአፈፃፀሙ ጉዳይ የወረዳው ፍ/ቤት በሰጠው

ትዕዛዝ ላይ ይግባኙ ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይቀርባል ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርስ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ከዚሁ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ እኩል ሆኖ የሚቆጠረው በማስፈፀም ረገድ ያለውን ሥልጣን በሚመለከት እንጂ ይግባኝ በተባለ ጊዜ እራሱ የተወከለው ፍ/ቤት በሚሰጠው ፍርድ ይግባኝ ሲባል ይግባኙን ለሚያየው ፍ/ቤት ነው በማለት ደንግጓል፡፡

**(አባሪ ቁጥር 6)**

የፍርድ አፈፃፀምን በተወከለው ፍ/ቤት ለጊዜው አግዶ ስለማቆየት በሚደነግገው ቁጥር 376 (1) ‹‹… እንዲሁም ፍርድ እንዲታገድለት ወይም ስለፍርዱ ወይም ስለውሳኔው አፈፃፀም ጉዳይ ለፈረደው ፍ/ቤት ሲያመለክት ፍርድ ቤቱ ፍርዱን እንደሚያስፈፅመው ፍ/ቤት ሆኖ ነገሩን ይመለከታል፡፡›› የሚለውን ከዚሁ ድንጋጌ የመጀመሪያ ክፍል ጋር አቀራኝተን ስንመለከተው ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡ ሆኖም ከእንግሊዝኛው ግልባጭ ጋር ተገናዝቦ ሲታይ ለአስፈፃሚው ፍ/ቤት በቂ ምክንያት የቀረበ እንደሆነ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን እንዲያግድለት ወይም ደግሞ እራሱ ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት አፈፃፀሙን ይዞት ቢሆን ኖሮ ስለአፈፃፀሙ መስጠት ይችል የነበረውን ማናቸውም ትዕዛዝ መስጠት እንዲችል የፍርድ ባለዕዳው ውሳኔውን ለሰጠው ፍ/ቤት ማመልከት እንዲችል በቂ ሆኖ ለሚገመት ጊዜ ብቻ ውሳኔው ከመፈፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ያደርግለታል የሚለውን ለማስተላለፍ ታስቦ እንደሆነ እንረዳለን፡፡

ይህም ፍርዱን የፈረደው ፍ/ቤት ሥልጣኑን ሙሉ በሙሉ አለማስተላለፉንና አስፈፃሚው ፍ/ቤትም ለዘለቄታው ማገድ የማይችል መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ድንጋጌው በእራሱ ግልፅ ባለመሆኑ የተነሣ አሻሚ ትርጉም ሊሰጥ በመቻሉ ለክርክር መራዘም ምክንያት ከሆኑ ድንጋጌዎች አንዱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 337 የተመለከተው ነው፡፡ ቁጥር 377 ***"ፍርድ በተፈረደለት በማናቸውም ሰው ላይ ፍርድ የተፈረደበት ወገን ክስ ያቀረበበት እንደሆነ ፍ/ቤቱ ተገቢ መስሎ የገመተውን በቂ ዋስትና ወይም መያዣ እንዲሰጥ ካደረገ በኃላ ለክርክሩ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ ፍርዱ ከመፈፀሙ ታግዶ እንዲቆይ ለማዘዝ ይችላል፡፡"*** በሚል በመቀረፁ አፈፃፀሙ ታይቶ

እንዲቆይ ትዕዛዝ የሚሰጠው የትኛው ፍ/ቤት ነው? የፍርድ ባለዕዳው በፍርድ ባለገንዘቡ ላይ ያቀረበውን ክስ እያየ ያለው ፍ/ቤት ወይስ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት? ለሚለው ጥያቄ ድንጋጌው ለብቻው ሲታይ አሻሚ ነው፡፡

በህግ አተረጓጎም መርህ መሠረት ህጉ አሻሚ መስሎ በታዩ ጊዜ ድንጋጌዎችን እርስ በእርሳቸው አስተሳስረን ልንተረጉም ይገባል፡፡ ይኸው ድንጋጌ የሚገኝበት ክፍል አፈፃፀምን ስለሚያስፈፅሙ ፍ/ቤቶች እና ስላላቸው ሥልጣን የሚገልፅ በመሆኑ በዚሁ ድንጋጌ "... ፍርድ ቤቱ... " የሚለው ሀረግ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት መሆኑን እንረዳለን ከዚህም በቀር ክስ የቀረበለት ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ የሚሰጥባቸው ሁኔታዎች በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154-159 በተመለከቱት ሁኔታዎች በመሆኑና የተጀመረን አፈፃፀምም አግዶ የሚያቆየው በዚሁ ህግ በቁጥር 332-335 በተመለከተው መሠረት የይግባኝ ክርክሩን የሚያየው ፍ/ቤት በመሆኑ በማናቸውም መንገድ ቢሆን የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 377 ድንጋጌ የፍርድ ባለዕዳው በፍርድ ባለመብቱ ላይ ክስ በማቅረቡ ምክንያት ክሱን እያየ ያለው ፍ/ቤት በሌላ ፍ/ቤት በፍርድ ባለዕዳው ላይ የተጀመረን የአፈፃፀም ክስ አግዶ ለማቆየት ሥልጣን የሚሰጥ አይደለም፡፡

## (አባሪ ቁጥር 7)

ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርብ ማመልከቻ በጊዜ የተገደበ ለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 384 ተመልክቷል፡፡ በቁጥር 385(1) "ፍርድ እንዲፈፀም የሚቀርበው ማመልከቻ ከዚህ በላይ ባሉት ቁጥሮች የተነገሩትን ግዴታዎችና ሥርዓቶች አሟልቶ የያዘ መሆኑን ፍርድ ቤቱ ማረጋገጥ አለበት፡፡" በማለት በመደንገጉና የይርጋ ጊዜው ሁኔታ ከቁጥር 385 በፊት የተቀመጠ በመሆኑ ጊዜው ያለፈበት የአፈፃፀም ጥያቄ ከሆነ እንደሌሎች የይርጋ ክርክሮች በተከራካሪ ወገን ብቻ እንዲቀርብ የተተወ ሳይሆን ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ሊያነሳው የሚገባ ጉደይ ነው፡፡ የጊዜውም መነሻ የሚታሰበው እንዲፈፀም የሚጠይቀው ነገር በፍርዱ ከተወሰነበት ቀንና ዓመተ ምህረት ጀምሮ ነው በሚል ተቀምጧል፡፡ ፍርድ ሲባል በመጀሪያ ደረጃ የተሰጠን ፍርድ ወይም በይግባኝ የተሰጠን ፍርድ ያጠቃላል የሚለውንም ጥያቄ የሚያስነሳ ነው፡፡

## (አባሪ ቁጥር 8)

የፍርድ አፈፃፀም መሠረታዊ ታሳቢዎችንና በአፈፃፀም ጊዜ የሚከሰቱ ችግሮች ምክንያቶቹ ምንድን ናቸው ለሚለው ጥያቄ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ጉዳዮች

ጠቋሚዎች ሲሆኑ ቀሪውን ክፍል ደግሞ ከሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የምናያቸው ይሆናል፡፡

## ጾምርታ በዋ በምርታ ማስወኸም ሂተ ስለሚሰጉ ባዕ ታ ዕዛዞ

ለጊዜው የሚሰጥ የማገድ ትዕዛዝ (temporary junction) ክርክሩ ተጀምሮ ነገሩ በፍርድ እስኪወሰን ወይም የተለየ ትዕዛዝ እስኪሰጥ ድረስ ያሉትን ሁኔታዎች በነበሩበት አኳኃን ጠብቆ ለማቆየት ሲባል ከሚሰጡት ጊዜያዊ ትዕዛዞች አንዱ ነው፡፡ ንብረት እንዳለ እንዲቆይ፣ ከመጥፋት እንዲድን፣ እንዳይበላሽ፣ ለሌላ ሰው ተላልፎ እንዳይሰጥ ወደ ሌላ ስፍራ እንዳይዛወር እንዳይባክን ለማድረግ ሲሆን ዓላማውም ክርክሩ ተጠናቆ የሚሰጥ ፍርድ ለአፈፃፀሙ ዋስትና እንዲኖረው፤ ውጤት እንዲያገኝ ለማስቻል ነው፡፡

ይህ ዓይነቱ ትዕዛዝ የሚሰጠውም ክሱን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ በሚያየው ፍ/ቤት ሲሆን ትዕዛዙ በሁለት ምክንያቶች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

አንደኛው በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 154(ለ) እንደተጠቀሰው ጊዜያዊ የማገጃ ተዕዛዝ የሚሰጠው በክርክሩ ምክንያት በሆነው ንብረት ላይ ሆኖ ይኸው ክርክር የተነሣበት ንብረት የሚጠፋ፣ የሚበላሽ ወይም ተከሳሹ በማናቸውም ምክንያት ለሌላ አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ መሆኑ በቃሉ መሃላ ሲረጋገጥ ሲሆን፤

ሁለተኛው ደግሞ ጊዜያዊ የዕግድ ትዕዛዝ ይሰጥበት የሚባለው ንብረት የክርክሩ ምክንያት (መነሻ) ባይሆንም ተከሳሹ የባለመብቶችን ጥቅም ለመጉዳት ሲል ንብረቱን ለማጥፋት፣ ለሌላ ሰው አሳልፎ ለመስጠት ያቀደ የዛተ ወይም ያሰበ መሆኑ የተረጋገጠ እንደሆነ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 157 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ጊዜያዊ የዕግድ ትዕዛዝ ከሳሹ በቃለመሃላ በሚያረጋግጠው አቤቱታ መነሻ በመሆኑ ተከሳሹ በቃለ መሃላ የተዘረዘሩት ፍሬ ነገሮች በእውነት ላይ የተመረኮዙ አይደለም በማለት የሚያስተባብል ከሆነ አስቀድሞ የተሰጠውን የዕግድ ትዕዛዝ ማስነሳት የሚቻልበት ሥርዓትም በቁጥር 158 ተቀምጧል፡፡

(አባሪ ቁጥር 9)

## በምርታ ማስወኸም ሂተ ብረ ስስማስጾበር

ፍርድ የተፈረደበት ወገን በቁጥር 386 እንደተደነገገው እንድ ፍርዱ የማይፈፀምበትን ምክንያት ካላስረዳ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 386(3) እና 392(1) መሠረት ፍርዱ እንዲፈፀም ወዲያውኑ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

ፍርድ የሚፈፀመውም የፍርድ ባለዕዳውን ንብረት በማስከበርና በማሸጥ ነው፡፡ የፍርድ ባለገንዘቡም በዚህ አኳኋን ይፈፀምለት ዘንድ ከላይ እንዳየነው ከፍርዱ በፊት ያሳገደውንም ሆነ ለፍርድ አፈፃፀም ሊውል ይችላል የሚለውን የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ዝርዝር ያቀርባል፡፡

በፍርድ አፈፃፀም ሂደት መንተት እንዳያስከትል እንዲያዝና እንዲሸጥ ተብሎ የቀረበው የንብረት ዝርዝር በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 ከተመለከቱት ውጭ መሆናቸውንና በእርግጥም በፍርድ ባለዕዳው ባለቤትነት የሚገኙ ስለመሆናቸው በሚቻለው መንገድ ሁሉ መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡

በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዲያዝና እንዲከበር የማድረጉ ተግባር አፈፃፀሙን በያዘው ፍ/ቤት ብቻ ሣይሆን በሌሎች ፍ/ቤቶችም ተይዞ እና ተከብሮ የተገኘ እንደሆነ ጉዳዩ በምን አኳኋን እንደሚታይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 413 ተመልክቷል፡፡ ቁጥር 413 “… ንብረቱ የተያዘው በፍ/ቤት የሆነ እንደሆነ ሌሎች ሦስተኛ ወገኖች ይህንኑ ንብረት አስቀድመን አስይዘናል፤ አስከብረናል በማለት የቀዳሚነት መብት አለን በማለት ክርክር ያነሱ እንደሆነ ክርክሩ የሚወሰነው ንብረቱን ይዞ በሚገኘው ፍርድ ቤት ነው፡፡” በማለት ደንግጓል፡፡

አንድ ንብረት አስቀድሞ በፍ/ቤት በመከበሩ ምክንያት የተፈረደ ፍርድ ሳይፈፀም ይቀራል ማለት እንዳልሆነ ይኸው ድንጋጌ አስረጂ ቢሆንም፤ ክርክሩ በየትኛው ፍ/ቤት ይታያል ለሚለው ግን ሁሉንም ጉዳይ የሸፈነ አይደለም፡፡

በመጀመሪያ ንብረቱን የያዘው የከፍተኛው ፍ/ቤና ሆኖ በተለያየ ምክንያት አፈፃፀሙ በመንተቱ የተነሣ በወረዳው ፍ/ቤት ውሣኔ መሠረት እንዲፈፀም የተከበረ

መሆኑ ቢታወቅ እንደ ቁጥር 413 ድንጋጌ ይዘት በባለገንዘቦች መካከል የሚነሳው የቀዳሚነት መብት ክርክር በወረዳው ፍ/ቤት ይታያል እንደማለት ነው፡፡

በእርግጥ ይህ አይነቱ ክርክር እንዳይከሰት በቁጥር 378/መ/ መሠረት አፈፃፀሙን ለከፍተኛው ፍ/ቤት ቢመራው የተመረጠ ይሆናል፡፡ ይህ ካልሆነ ግን ድንጋጌው ቀጥተኛ ምላሽ አይሰጥም፡፡

ፍ/ቤቶቹ አቻ ከሆኑ ችግር የሚያስከትል መስሎ አይታይም፡፡ ላይና ታች ከሆኑ ግን ድንጋጌው ትርጉም ያሻዋል፡፡ ይኸው ድንጋጌ የተወሰደው ከህንድ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 63 እንደሆነ ከይዘቱ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ የህንድ ድንጋጌ የአቻነት ሥልጣን ባላቸው ፍ/ቤቶች ንብረቱ ተከብሮ በሚገኝበት ጊዜ ቀድሞ ንብረቱን ባስከበረው ፍ/ቤት፤ የሥልጣን ደረጃቸው እኩል ባልሆነ ፍ/ቤቶች ንብረቱ ተከብሮ በሚገኝበት ጊዜ ደግሞ ሥልጣኑ ከሁሉም ከፍ ብሎ በሚገኘው ፍ/ቤት ክርክራቸው ታይቶ እንደሚወሰን ተመልክቷል፡፡ የቁጥር 413 ድንጋጌ በዚህ መሠረት ተብራርቶ የተቀረፀ ባለመሆኑ ላላስፈላጊ ሙግቶች በር ከፋች ነው፡፡

**(አባሪ ቁጥር 10)**

ክርክሩን አይቶ ለመወሰን የሚችለው ፍ/ቤት የትኛው እንደሆነ ከተለየ በኋላ ጉዳዩ ታይቶ የሚወሰነው በፍ/ብ/ሥ/ሕ/ቁ 403 መሠረት ነው፡፡

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403 በአንድ የፍርድ ባለዕዳ ላይ ቁጥራቸው ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የፍርድ ባለገንዘቦች በቀረቡ ጊዜ እና የሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች ፍላጐት ይኸው የፍርድ ባለዕዳው ንብረት/ገንዘብ የማይሸፍን ሆኖ በተገኘ ጊዜ የፍርድ ባለዕዳን ሃብት እንዴት ማከፋፈል እንደሚቻል የሚሸፍን ክፍል ነው፡፡
የድንጋጌው ዓላማም ሁለት ገፅታ አለው፡፡

1ኛ/ አላስፈላጊ የሆነና የተነጣጠለን የአፈፃፀም ክስን ለማስቀረት፣

2ኛ/ ሁሉንም ገንዘብ ጠያቂዎች በእኩል ደረጃ በማስቀመጥ ፍትሃዊ የንብረት ክፍፍል ለማድረግ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በተለያዩ የሕግ ክፍሎች እንደተደነገገው ሁሉም ገንዘብ ጠያቂ በእኩል ደረጃ ይገኛል ማለት አይደለም፡፡

- በተወሰኑ ጉዳዮች መንግስት ባለገንዘብ ሆኖ በተገኘ ለዜጐች የሚሰጠውን ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የደህንነት አገልግሎት በማየት፣
- በደሞወዝ ምክንያት ባለገንዘብ የሆነ ወገን ካለ ደሞወዝ የቤተሰብ መተዳደሪያ፣ ሕልውና በመሆኑ
- ለግዴታ ማስፈፀሚያ መያዣ አስቀድሞ ያገኘ ባለመብት ከሆነ የመያዣ ግቡ ለዕዳ ማስፈፀሚያ ዋስትና መሆኑ ታሪካዊና ልማዳዊ መሆኑን በማየት ሕግ አውጭው በተለያዩ እና አግባብነት ባላቸው ሕጐች የቀዳሚነት መብት ያላቸው መሆኑን አረጋግጧል፡፡ ስለሆነም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 403 ድንጋጌ ተፈፃሚነቱ የቀዳሚነት መብት በሌላቸውና በተራ ባለገንዘቦች መካከል የተወሰነ ነው ማለት ይቻላል፡፡ እያንዳንዱም ተራ የገንዘብ ጠያቂ ከፍርድ ባለዕዳው ጠቅላላ ሃብት ባለፈረደው የገንዘብ መጠን /Rateably/ እንዲከፋፈል ይደረጋል፡፡

ከዚህ በቀር የቀዳሚነት መብት አለን የሚሉ ወገኖች በቀረቡ ጊዜ ከላይ እንደተመለከተው ጉዳዩ የሚታየው አግባብነት ባላቸው ድንጋጌዎች መሠረት ይሆናል፡፡

በአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 167 *"በቅጥር ላይ ከተመሠረተ የሥራ ግንኙነት የሚመነጭ ማንኛውም የሠራተኞች የክፍያ ጥያቄ ከማናቸውም የክፍያ ወይም የዕዳ ጥያቄ ቅድሚያ ይኖረዋል፡፡"* በማለት የዕዳ ክፍያ ቅድሚያነቱን የደነገገ በመሆኑ እንደ ሕጉ አነጋገር ከሌሎች ገንዘብ ጠያቂዎች ቀድሞ እንደ ፍርድ እንዲፈፀም የማድረግ መብት አለው፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ 80/1/ *"ዋስትና የተሰጣቸው የሌሎች አበዳሪዎች የቅድሚያ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት ግብር ተከፋይ ከሚሆንበት ቀን አንስቶ ተከፍሎ እስካለቀበት ጊዜ ድረስ ግብር የመክፈል ግዴታ ባለበት ሰው ሃብት ላይ ባለሥልጣኑ ከማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች የቀደምትነት መብት ይኖረዋል፡፡"* በማለት የተደነገገ በመሆኑ በመያዣ ምክንያት በፍ/ብሔር ሕጉ ከቁጥር 3059 እና ተከታዮች የተሰጠው የቀዳሚነት መብት የተጠበቀ መሆኑን ያስረዳል፡፡ ስለሆነም ባለመያዣ የሆነው የፍርድ ባለመብት በግብር ምክንያት ባለመብት ከሆነው ከመንግስት ቀድሞ ዕዳውን የመሰብሰብ መብት ያለው መሆኑን ያስረዳል፡፡ የአዋጅ ቁጥር 286/94 አንቀጽ ጥቅል አባባል የያዘ 80 "... ለማናቸውም ሌሎች ዕዳዎች ..." የሚል

ጥቅል አባባል የያዘ ሐረግ ስለሰፈረበት በአዋጅ ቁጥር 377/96 ቁጥር 167 ጋር ይቃረናል፡፡ እንደዚህ በሆነ ጊዜ በዕኩል ደረጃ የሚገኙ ሕጐች አንድን ጉዳይ በተለያየ መንገድ ደንግገው በተገኙ ጊዜ በዚህም የተነሣ ሕጐቹ እርስ በእርሳቸው ከተቃረኑ በኋላ የወጣው ሕግ ከበፊተኛው በልጦ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡ በሚለው የሕግ አተረጓጐም መርህ መሠረት በአሠሪና ሠራተኞች ጉዳይ የሚጠየቀው የዕዳ ክፍያ ጥያቄ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

**(አባሪ ቁጥር 11)**

**<u>ስለማይከበሩና በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ስለማይወሰዱ ሀብቶች</u>**

ፍርድ የሚፈፀመው የባለዕዳውን ንብረት በማስከበርና በማሸጥ ቢሆንም ፍርድን ለማስፈፀም ሲባል የማይከበሩና በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት ሊወሰዱ የማይችሉት ንብረቶች ዓይነትና መጠን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404 ሥር ተዘርዝረዋል፡፡ ከሚከተሉት ሁለት ንዑስ አንቀጾች በስተቀር ድንጋጌው በእራሱ ግልፅ በመሆኑ ማብራሪያ የሚያስፈልገው መስሎ አይታይም፡፡

በቁጥር 404/ለ/ "ለዕለት ሞያ ሥራዎቹ አገልግሎት ለንግድ ሥራው ማከናወኛ ተገቢ የሆኑ ዕቃዎች ከሚለው ድንጋጌ "ዕቃዎች" የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም ሊያሰጥ በሚችል አኳኋን ይጠቀስ እንጂ የዚሁ ግልባጭ ከሆነው የእንግሊጨኛ ንባብ ጋር አጣቅሰን ካየነው ተገቢ የሆኑ የመገልገያ መሣሪያዎች ለማለት ተፈልጐ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ በንዑስ ፊደል ሠ "ለጡረታው የሚከፈለው ገንዘብ ..." የሚለውን ድንጋጌ ስለጡረታ ጉዳይ ከደነገገው የጡረታ ሕግ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 45 ጋር ተገናዝቦ ሊታይ የሚገባው ነው፡፡

ለጡረታው የሚከፈለው ገንዘብ እንደማይከበር በፍርድ አፈፃፀም ምክንያት እንደማይያዝ በቁጥር 404 የተገለፀ ቢሆንም በመንግስት ሠራተኞች ጡረታ አዋጅ ቁጥር 345/95 አንቀጽ 45 ላይ ከዚህ በተለየ ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ይኸውም በአንቀጽ 45 ከጡረታ አበሉ እንዲከፈል የተጠየቀው ዕዳ ለመንግስት ገቢ የሚሆን መቀጮ፣ ግብር ወይም ቀረጥ ለመክፈል ወይም አግባብ ባላቸው የፍ/ብሔር ድንጋጌዎች መሠረት የተወሰነ ቀለብ የመስጠት ግዴታ ለመወጣት በፍርድ ቤት የታዘዘ እንደሆነ የጡረታ አበሉ ሊከበር እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

የጡረታ አበል በዕዳ ምክንያት ሊከበር እና ሊያዝ የሚችል የመሆኑና የአለመሆኑ ጉዳይ በተለያዩ ሕጐች በተለያዩ ሁኔታ ተደንግጐ ከተገኘ በሕግ አተረጓጐም ዘዴ መሠረት ስለጡረታ ጉዳይ በተለይ የሚደነግገው የጡረታ አዋጁ በመሆኑ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በልጦ ተፈፃሚነት ሊኖረው የሚችል ከመሆኑም በላይ በኊላ የወጣ እንደመሆኑ ተፈፃሚነት የሚኖረው ይኸው የጡረታ ሕግ ነው ወደ ሚለው መደምደሚያ ሊያደርሰን ይችላል፡፡

የጡረታ አበል በፍርድ ምክንያት ሊያዝ አይገባውም የተባለው መተዳደሪያው በመሆኑ ነው፡፡ ለመተዳደሪያው ሲል ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ለማግኘት ሲል ባመጣው ዕዳ ምክንያት ፍርድ አርፎበት ከተገኘ ይህንኑ ዕዳ ለማስፈፀም የጡረታ አበልን ማስከበር ምን ይከለክላል? የቁጥር 404/ሠ/ ድንጋጌ ይህን ጉዳይ ሊሸፍን የሚችል አይደለም የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል፡፡ በተለይም ይህንኑ ጥያቄ ለአብነት ያህል ከተሻሻለው የፌዴራል የቤተሰብ ሕግ አዋጁ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 205/3/ ". . . ለቀለብ ተቀባዩ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ነገር ለማግኘት ሲባል የመጣ ዕዳ መሆኑ ከተረጋገጠ የቀለብ ገንዘብ ሊተላለፍና ሊያዝ እንደሚችል ከተደነገገው ጋር ተገናዝቦ ከታየ የቀለብ ገንዘብ ማለት ለጡረታ የሚከፈል ገንዘብ እስከሆነ ድረስ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 404/ሠ/ ገዳቢ የሆነ ድንጋጌ መስሎ አይታይም፡፡

## <u>በተከበረ ንብረት ላይ የሚቀርብን አቤቱታ ስለመመርመር /418 — 421/</u>

ለአፈፃፀም ክስ መዘግየት ዐበይት ከሆኑት ምክንያቶች አንዱ በአፈፃፀም ምክንያት ንብረት እንዳይያዝ ወይም እንዳይከበር በሚቀርበው አቤቱታ መነሻ የሚደረገው ክርክር ነው፡፡

ይኸው አቤቱታ ያለበቂ ምክንያት ሳይዘገይ ከቀረበ እና ተቃዋሚው ወይም መብት አለኝ ባዩ በተያዘው ወይም በተከበረው ንብረት ላይ ያለውን የቀዳሚነት መብት ወይም ባለይዞታነቱን የሚያረጋግጥ የፅሑፍ ማስረጃ አያይዞ ማቅረቡ ከተረጋገጠ አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ጉዳዩን ይመረምራል፡፡ በአቤቱታው መነሻ ጉዳዩ ሊመረመር ይገባል ከተባለ የተከበረው ንብረት የማን ነው? የፍርድ ባለዕዳው ወይስ መቃወሚያ ያቀረበው ነው? ወደ ሚለው ክርክር ማምራቱ አይቀሬ ነው፡፡ ለዚህም ነው አቤቱታ

አቅራቢው ወይም ተቃዋሚው በመጀመሪያው ክስ ተካፋይ እንደሆነ በመቁጠር አፈፃፀሙን የያዘው ፍ/ቤት ጉዳዩን መመርመር አለበት በሚል የተቀመጠው፡፡

በዚህ ረገድ ጉልተው ከሚታዩት ክርክሮች መካከል የፍርድ ባለዕዳው ሚስት/ባል ለፍርድ ምክንያት የሆነው ተግባር የተፈፀመው ወይም ዕዳው የመጣው እኔ ሳላውቀው በመሆኑ ለጉዳዩ አግባብነት ባለው የቤተሰብ ሕግ መሠረት አንደኛው ተጋቢ በግሉ በመጣው ዕዳ ምክንያት በጋራ ሃብታችን ላይ አፈፃፀም ሊቀጥል አይገባም፡፡ ይህ እንኳ ቢታለፍ ድርሻ ሃብቴ ሊነካብኝ አይገባም በሚል የሚቀርበው አቤቱታ ነው፡፡

ለዚሁ ዓይነት ክርክር አግባብነት ያለው የቤተሰብ ሕግ በአንድ በኩል የሰለጠ የሥራ/የንግድ እንቅስቃሴ /Business transaction/ እንዲኖር በመፈለግ፤ በሌላ በኩል በትዳር ምክንያት የተፈጠረን የጋራ ሃብት ላይ ጥበቃ በማድረግ ረገድ ያለውን ሚዛን በማጣጣም የተቀረፀ መሆኑ ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

**(አባሪ 12)**

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት አቤቱታ የሚያቀርቡት ወገኖች የተከራካሪ ወገኖችን ማንነት በመለየት የክርክርን አድማስ በመወሰን በኩል በተቀመጡት ድንጋጌዎች /በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 41, 42, 358 . . ./ መሠረት የክርክሩ ተካፋይ መሆን የሚገባቸው ወገኖች ከሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 418 መሠረት ገብተው በመከራከር መብት አላቸው ወይስ የላቸውም? የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡

**(አባሪ ቁጥር 13)**

**<u>የሐራጅ ሽያጭ ሥነ - ሥርዓት</u>**

በቀጥታ ወይም በተለዋዋጭ ገንዘብ እንዲከፈል የተሰጠ ማናቸውም ፍርድ ወይም ውሣኔ የሚፈፀመው የባለዕዳውን ንብረት በማስከበርና በማሸጥ ሲሆን፤ ማናቸውም ሃብት ወይም ንብረት የሚሸጠውም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 422/3/፣ 427 እና 439 የተመለከቱት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የሐራጅ ሽያጭ በማድረግ ነው፡፡

ለፍርድ ማስፈፀሚያ ተብሎ የሚሸጠውም ንብረት በቁጥር 394/2/ እና 422/1/ እንደተደነገገው ከሚፈለገው የዕዳ መጠን ጋር በተቻለ መጠን ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ በተከታዩ እንደምናየው ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428/2/ ጋር ተያይዞ የሚነሳውን ችግር ለማስቀረት ይረዳል፡፡

**<u>ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 428 ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚታዩ ችግሮች</u>**

ይኸው ድንጋጌ ለትርጉም በር በሚከፍት ሁኔታ የተቀረፀ ከመሆኑ የተነሣ ድንጋጌውን በሥራ ላይ በማዋል ረገድ ከፍርድ ቤት ፍርድ ቤት አልፎ አልፎም በአንድ ፍ/ቤት በሚገኙ የተለያዩ ችሎቶች ለድንጋጌው የተለያዩ ትርጉም በመስጠት በተመሣሣይ ጉዳይ የተለያዩ ውሣኔ ሲሰጥ ይስተዋላል፡፡

ለዚህም ወጥ ያልሆነ አሠራር እንደ ምክንያትነት የሚወሰደው በቁጥር 428/1/ "በዚህ ሕግ በቁጥር 423/2/ በተመለከተው መሠረት በሚሰጠው ማስታወቂያ የተገለፀውን የዋጋ ግምት የሚከፍል ገዥ ያልተገኘ እንደሆነ ድጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት ሁለተኛ ጨረታ ይደረጋል፡፡" ከሚለው ፓራግራፍ "በማስታወቂያ የገለፀውን የዋጋ ግምት የሚከፍል <u>ገዥ ያልተገኘ</u> እንደሆነ . . ." የሚለው አባባል ለመግዛት ተጫራቾች ቀርበው ነገር ግን የግምቱን መነሻ ዋጋ ባለመጥራታቸው ነው? ወይስ ጭራሹኑ የሐራጅ ሽያጩ በሚደረግበት ጊዜና ቦታ ተጫራች ባለመገኘቱ? ለሚለው ጥያቄ ቀጥተኛ ምላሽ የማይሰጥ በመሆኑ ነው፡፡

በተለይም የመጀመሪያ ደረጃ ሽያጭ ተደርጐ ገዥ አልተገኘም ከሚል መደምደሚያ ላይ ከተደረሰ በሁለተኛ ሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ንብረቱ የሚሸጠው ከግምቱ ዋጋ በታች ቢሆንም ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ገዥ በመሆኑ ከላይ የተቀመጠውን ጥያቄ ይበልጥ የተወሳሰበ ያደርገዋል፡፡

“. . . Where the highest bid at a sale by auction . . .” የሚለው የእንግሊዘኛ ግልባጭ በሐራጅ ሽያጭ ጊዜ በጨረታ የተገኘው ከፍተኛ ዋጋ በማለት የተቀመጠ በመሆኑ በመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ ገዥዎች ቀርበው ውድድር ያደረጉ መሆኑን ነገር ግን ከግምቱ መነሻ በታች የሆነ የግዥ ዋጋ በማቅረባቸው ምክንያት ሽያጩ ሊከናወን ያልቻለ መሆኑን የሚያመለክት ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ለተለያዩ አተረጓጎም ምክንያት ሆኖ ይገኛል፡፡

የ1958ቱ ዓ.ም የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ከመውጣቱ በፊት በነበረው የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 176/45 አንቀጽ 22 ደግሞ “በዚህ ደንብ እንደተመለከተው በአደባባይ በሚደረገው የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ <u>ተጫራቾች ያቀረቡት ከፍተኛ ዋጋ</u> በመሐንዲሱ ወይም ግምት አዋቂው ሰው ወይም ጉባኤው ከገመተው ዋጋ ያነሰ እንደሆነ . . . የሽያጩ ማስታወቂያ እንደገና ይደገማል፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በድጋሚው የሐራጅ ሽያጭ ጊዜ በጨረታ የቀረበው ከፍተኛ ዋጋ ከግምቱ ቢያንስም በዚያው በቀረበው ዋጋ ይሸጣል፡፡” በሚል ተደንግጎ የነበረና ይህም የበፊተኛው ሕግ ይዘት አሁን በሥራ ላይ ካለው ሕግ የእንግሊዘኛ ግልባጭ /version/ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ መገኘቱ /የአማርኛው ግልባጭ ገዥነት ያለው ድንጋጌ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ድንጋጌው ትርጉም የሚያሻው መሆኑን አመላካች ነው፡፡

በመሆኑም ከትርጉም ሥራ የተነሣ ሊነሱ የሚችሉትን የክርክር መስመሮች /የመከራከሪያ ሐሳቦች/ እንመልከት፡፡

<u>አንደኛው</u>፡- በቁጥር 423/2/ በተመለከተው መሠረት በሚሰጠው ማስታወቂያ የተገለፀውን የዋጋ ግምት የሚከፍል ገዥ ካልተገኘ ድጋሚ ማስታወቂያ በማውጣት ሁለተኛ ጨረታ እንደሚደረግና ንብረቱም የሚሸጠው በሁለተኛ ጨረታ ጊዜ ከፍተኛ ዋጋ ለሚያቀርብ ተጫራች እንደሆነ በግልፅ ተመልክቷል፡፡ ስለሆነም “ . . . የሚከፍል ገዥ ያልተገኘ እንደሆነ . . .” የሚለው አባባል በመጀመሪያው ሐራጅ ጊዜ ተጫራች የግድ መቅረብ እንዳለበት የሚያመለክት አይደለም፡፡

በተደረገው ጥሪ መሠረት በዋጋው መነሻ ንብረቱን የሚገዛ ተጫራች በግንባር ካልቀረበ የመጀመሪያ ሐራጅ እንደተደረገ መቆጠር አለበት፡፡ አለበለዚያ የመጀመሪያ ሐራጅ ተደርጓል ለማለት ተወዳዳሪ ቀርቦ ፉክክር ከተደረገ በኋላ በማስታወቂያው ላይ

የተገለፀውን የዋጋ ግምት የሚከፍል ገዥ ያልተገኘ እንደሆነ ብቻ ነው የምንል ከሆነ ተወዳዳሪ እስከሚቀርብ ድረስ ለምን ያህል ጊዜ ነው፡ የመጀመሪያ ማስታወቂያ እያልን ተከታታይ ትዕዛዝ የምንሰጠው? መዳረሻውስ የት ነው? ባለዕዳ ዕዳውን እንዲከፍል ባለገንዘቡም ገንዘቡን እንዲያገኝ ማድረግ ይቻል ዘንድ ከፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማስ አንፃር ይኸው አካሄድ ይደገፋል ወይ? በመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ የሚደረገው የሽያጭ ግብዣ በቁጥር 423/2//ሀ/ መሠረት በተቀመጠው የዋጋ መነሻ እስከሆነ ድረስ ከዚህ ዋጋ በታች ለመጥራት ሲሉ የሚቀርቡት ተጫራቾች ከእነ አካቴው /ጭራሹኑ/ ካልቀረቡትስ በምን ይለያሉ፡፡ በመሆኑም በመጀመሪያው የጨረታ ማስታወቂያ መሠረት ተወዳዳሪ ቀርቦ በማስታወቂያው ላይ የተገለፀውን የዋጋ ግምት ሊከፍል አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን በማስታወቂያው በተገለፀው ጊዜና ቦታ ጭራሹኑ ገዥ ካልተገኘ የመጀመሪያ ሐራጅ እንደተደረገ በመቁጥር ድጋሚ የጨረታ ማስታወቂያ በማውጣት ሁለተኛ ጨረታ መደረግ አለበት፡፡ ንብረቱም የሚሸጠው ከንብረቱ ግምት ዋጋ በታች ቢሆንም ከፍተኛ ዋጋ ላቀረበው ተጫራች ነው የሚለው ነው፡፡

<u>ሁለተኛው</u> **የክርክር መስመር ደግሞ፡-**

በድንጋጌው የእንግሊዘኛ ግልባጭ "በጨረታ የተገኘው ከፍተኛ ዋጋ . . ." የሚለውን ሐረግና የመጀመሪያ ጨረታ ተደርጓል ካልን የሚያስከትለውን ውጤት መነሻ የሚያደርግ ነው፡፡

". . . በጨረታ የተገኘው ከፍተኛ ዋጋ . . ." የሚለው አነጋገር ተወዳዳሪ ቀርቦ ጨረታ የተከናወነ መሆኑን ነገር ግን አሸናፊው የግምቱን መነሻ ዋጋ የሚከፍል ሆኖ አለመገኘቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ስለሆነም ንብረቱን በሐራጅ ለማሸጥ ማስታወቂያ በመጣበት ቀን አንድም ተጫራች ሳይቀርብ ቢቀር ንብረቱ በሐራጅ እንደሚሸጥ ለሕዝብ በማስታወቂያ መግለፅ ብቻውን የመጀመሪያ ጨረታ እንደተደረገ አያስቆጥርም፡፡ የመጀመሪያ ጨረታ ሳይኖር ሁለተኛ ጨረታ ለማለት አይቻልም፡፡ በመጀመሪያው የሐራጅ ሽያጭ ማስታወቂያ ላይ በተገለፀው ጊዜና ቦታ ተጫራች ሳይቀርብ ቀርቶ በድጋሚ ማስታወቂያ መሠረት ተጫራች ቢቀርብ ጨረታው የመጀመሪያ ነው ከሚባል በስተቀር ሁለተኛ ጨረታ ሊባል አይችልም፡፡ በዚህ ጊዜ ንብረቱም የሚሸጠው የዋጋውን ግምት መነሻ በማድረግ ነው፡፡

**(አባሪ ቁጥር 14)**

በሁለተኛው ጨረታ ማስታወቂያ ላይ በተወሰነው ቀን ተጫራች ያልቀረበ እንደሆነ ማናቸውም ተቃራኒ ድንጋጌ ቢኖርም እንኳ ይህን ንብረት የፍርድ ባለገንዘቡ ተረክቦ እንዳይዝ ማድረግ እንደሚቻልና ይህም በሆነ ጊዜ እንደነገሩ አካባቢ ሁኔታ ዕዳው በሙሉ ወይም በከፊል እንደተፈፀመ እንደሚቆጠር በቁጥር 428 ንዑስ ቁጥር 2 ውጤቱ ተቀምጧል፡፡ በቁጥር 423/1/ መሠረት የሚሸጠው ንብረት የሚጠየቀውን ዕዳ ለመሸፈን የሚያስችለውን ክፍል መሆኑን በማረጋገጥ፤ ወይም ደግሞ በቁጥር 394/2/ መሠረት በአፈፃፀም እንዲሸጥ የተባለው ንብረት በተቻለ መጠን በፍርዱ ላይ ከተገለፀው የገንዘብ ልክ ጋር ተመዛዛኝ መሆኑን በማየት የአሻሻጥ ሥርዓቱን የምንከተል ከሆነ በቁጥር 428/2/ መሠረት እንዲፈፀም የማድረጉ ተግባር ተከታይ ችግር ሊያስከትል አይችልም ማለት ይቻላል፡፡ ነገር ግን ይህንኑ ሥርዓት ካልተከተልንና የንብረቱ ግምት በልጦ የሚፈለገው ዕዳ አነስተኛ ከሆነ ስለዕዳው ባለገንዘቡ ንብረቱን እንዲረከበው የማድረጉ አሠራር በባለዕዳው ዘንድ ፍትህን ያጓድላል፡፡ በንብረቱ ግምት እና በሚፈለገው ዕዳ መጠን መካከል ያለውን ልዩነት የፍርድ ባለመብቱ በጥሬ ገንዘብ ለባለዕደው ይከፈለው እንዳይባል ባለገንዘቡ ያስፈረደውን በገንዘብ መሰብሰብ እንጂ ከፈቃዱ ውጭ ግዥ ለመፈፀም የቀረበ ባለመሆኑ ላልታሰበ ዕዳ ሊዳርገው በሚችል አኳኋን ያልፈለገውን ንብረት ተረክቦ እንደገና ገንዘብ እንዲመልስ ማድረጉም ፍትሃዊ አይሆንም ስለሆነም እንደዚህ ዓይነት ችግር እንዳይከተል የአሻሸጥ ሥርዓቱን መነሻ እንደህጉ አነጋገር መስመር ማስያዝ ያስፈልጋል፡፡ ይህ ታልፎ ከዚህ ደረጃ የምንደርስ ከሆነ ግን ከተቻለ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 439 መሠረት እንዲፈፀም ማድረግ፤ ይህ የማይሆን ከሆነ በቁጥር 428/2/ የተመለከተው ድንጋጌ ፈቃጅ እንጂ አስገዳጅ ባለመሆኑ በፍ/ቤቱ አስተያየት ሌሎች አማራጮችን ከመፈለግ በስተቀር እንደ ቁጥር 428/2/ የግድ መፈፀም አለበት ወደ ሚለው መደምደሚያ የሚያደርሰን መስሎ አይታይም፡፡

**(አባሪ ቁጥር 15)**

## የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ጉዳዮች በነፃ ስለሚታዩበት ሁኔታና ሕገ መንግሥቱ

የዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ዋነኛ ዓላማው ፍ/ቤቱ እንደማንኛውም አገልግሎት ሰጭ የመንግስት ተቋም ለሚሰጠው የዳኝነት አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን እግረ መንገዱንም የዳኝነት ገንዘብ በክሱ በተጠየቀው የገንዘብ ወይም ሀብት መጠን መሠረት የሚከፈል በመሆኑ መብትን መነሻ ያላደረገ ተገቢ ያልሆነ ክስ እንዳይቀርብ እንዲሁም ያለአግባብ በእጅጉ ተጋኖ የሚቀርብን ክስ መገደብንም ታሣቢ ያደረገ ነው፡፡

ይሁን እንጂ ይህ የዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ክስ ለሚያቀርቡ ወገኖች ሁሉ ቋሚ ቅድመ ሁኔታ ነው ማለት አይደለም፡፡ የዜጐችን አመኔታ ያተረፈ የዳኝነት አካል ተቋቁሟል ለማለት ከሚያበቁት ማሚያዎች አንዱ የዳኝነት አካሉ ተደራሽ ሆኖ መደራጀቱ ሲረጋገጥ ነው፡፡ የዳኝነት አካሉ ተደራሽ ነው ከሚልባቸው ሁኔታዎች አንዱ ፍ/ቤቱ ለሚሰጠው የዳኝነት አገልግሎት በተመላሽ ሊከፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ለመፈፀም አቅም የሌላቸው ወገኖች ክሳቸውን ያለክፍያ እንዲያቀርቡ የሚያስችል ሥርዓት ሲዘረጋ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 37/1/ "ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍ/ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ሥልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሣኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡" በማለት ፍትሕ የማግኘት መብት ተረጋግጧል፡፡ ይህም መሠረታዊ የሆነው መብት በገንዘብ አቅም ማነስ ምክንያት ሊሸረፍ የሚችልም አይደለም፡፡

ከዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ሥርዓት አስፈላጊነት አንፃር በዝርዝር ሕጉ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 215 "የሚቀርቡት ክሶች ሁሉ የዳኝነት ገንዘብ ካልተከፈለባቸው በቀር ተቀባይነት አያገኙም" በማለት በመርሕ ደረጃ ከደነገገ በኋላ የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል በነፃ ክስ የማቅረብ ደንብ የተነገረው ድንጋጌ የተጠበቀ ነው፡፡ በማለት በተለየ ሁኔታ የተደነገገውም ይህንኑ መሠረተ ሃሣብ ምርኩዝ ያደረገ ነው፡፡ ዝርዝር አፈፃፀሙን የተመለከተን እንደሆነ፡-

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 467/1/ “. . . ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ ገንዘብ የሌለውና ለማግኘት የማይችል ማናቸውም ድሃ ሰው የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍል ነፃ ፋይል ከፍቶ ክስ ለማቅረብ ይችላል፡፡ በማለት የተደነገገ ቢሆንም በየክልሎች ማሕበራዊ ፍ/ቤትን ለማቋቋም ከወጣው አዋጅ አንፃር ሲታይ የዚሁ ሥርዓት የተሟላ አፈፃፀም በፌዴራል ፍ/ቤቶች የተወሰነ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ለማሕበራዊ ፍ/ቤቶች ከተሰጣቸው ሥልጣን አንዱ በመንግስት አካላት ለሚሰጥ ነፃ አገልግሎት የአመልካቹን የኑሮ ሁኔታ በማረጋገጥ የድህነት ማስረጃ መስጠት ነው፡፡ ፍ/ቤትም አገልግሎት ከሚሰጡት የመንግስት ተቋማት አንዱ በመሆኑ የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል በነፃ ክስ ማቅረብ ይቻል ዘንድ ማረጋገጫ የሚሆነው ማስረጃ በማሕበራዊ ፍ/ቤት ታይቶ የሚሰጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በማሕበራዊ ፍ/ቤት የሚሰጠው ማስረጃ ስለድህነቱ ጉዳይ የመጀመሪያ ደረጃ አስረጂ እንጂ ያለቀለት ወይም ደምዳሚ ማስረጃ /Conclusive Evidence/ ሆኖ ሊወሰድ አይገባውም፡፡ ምክንያቱም የድሀ ደንብ ክስ አቀራረብ የእራሱ የሆነ የተሟላ ሥርዓትን የሚከተል በመሆኑ ነው፡፡

በቁጥር 467 እና ተከታይ ድንጋጌዎች እንደተመለከተው በድሃ ደንብ እንዲታይ ክሱ የቀረበለት ፍ/ቤት የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱ ቀርቦ እንዲታይ ከመፍቀዱ በፊት ክሱ የሚያስከስስ መሆኑንና አለመሆኑን፤ የሚያስከስስ ነው ከተባለም አመልካቹ ድሃ መሆኑንና አለመሆኑን አስመልክቶ በግራ ቀኙ በኩል የሚቀርቡትን ማስረጃዎች ከሰማ በኋላ ነው ማስረጃ የሚሰጠው፡፡ በማሕበራዊ ፍ/ቤት በኩል ይኸው ሥርዓት የሚፈፀም አይደለም፡፡ ጥያቄው የሚቀርበውና ማስረጃው የሚሰማው በአንዱ ወገን ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም ተከሣሹ የከሣሽን የክስ ማመልከቻና በማሕበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠን የድህነት ማስረጃ ተመልክቶ ከሳሽ ለፍ/ቤት መክፈል የሚገባውን የዳኝነት ገንዘብ ለመክፈል የሚያስችለው አቅም አለው የሚል ከሆነ በመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያነት አንስቶ ይከራከርበታል፡፡ ፍ/ቤቱም በዚሁ አከራካሪ ነጥብ ላይ የግራ ቀኙን ማስረጃ ሰምቶ ይወስናል፡፡

ድሃ ማን ነው? ለሚለው ጥያቄ ቁጥር 467 “ . . . *ገንዘብ የሌለውና ለማግኘት የማይችል ማናቸውም ድሃ ሰው . . .”* በሚል ከማስቀመጡ በቀር ሌላ መስፈርት አለበጀለትም፡፡ በእርግጥ በቁጥር 468/1/ መሠረት አመልካቹ እንደ ጥያቄው ድሃ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ለመለየት፡-

- የአመልካቹ ሥራ ወይም ሙያ፣
- ገቢ ካለው የገቢው መጠን፣
- ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስ ንብረት ካለው
- በኪራይ የሚኖር ከሆነ የሚከፍለው የኪራይ መጠን
- ማግባቱንና አለማግባቱን

ከሚያስተዳድራቸው የቤተሰብ ብዛት አንፃር በማገናዘብ የሚገኝበትን የገንዘብ አቋም በመለየት እና ሊከፈል ከሚገባው የዳኝነት ገንዘብ መጠን ጋር በንፅፅር በማየት የሚወሰን እንጂ ቁርጥ ያለ መደምደሚያ ላይ መድረስ አይቻልም፡፡

ይሁን እንጂ በድሃ ደንብ ክስ እንዲታይለት ጥያቄ የሚያቀርብ ወገን ከቀረበው ክስ ዝርዝር ሁኔታ ፍ/ቤቱ ድሃ ያለመሆኑን ከተረዳ ተከሳሹ ከመጠራቱም በፊት ቢሆን በእራሱ አነሳሽነት በማህበራዊ ፍ/ቤት የተሰጠው ማስረጃ የሚታመን አይደለም፤ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

## (አባሪ ቁጥር 16)

ሌላው ከዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ነጥብ በድሃ ደንብ ክስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት ከሳሽ በፍ/ብ/ሥ/ሥሕ/ቁ 200 መሠረት በቂ መያዣ ወይም ዋስ እንዲጠራ ማስገደድ ይቻላል ወይስ አይቻልም? የሚለው ነው፡፡

ክርክሩ ለሚያስከትለው ወጭና ኪሣራ ፍ/ቤቱ በእራሱ አነሳሽነት ወይም ተከሳሽ ማመልከቻ ሲያቀርብለት የነገሩን ሁኔታ በማየት ክስ ያቀረበው ወገን በቂ መያዣ እንዲያቀርብ ማድረግ እንደሚችል በቁጥር 200 ሥር ተደንግጓል፡፡

የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፍል በነፃ ክስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት ከሣሽ በዚሁ ድንጋጌ መሠረት በቂ መያዣ እንዲያስይዝ ወይም ዋስ እንዲጠራ ማዘዝ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ስለገንዘቡ አቋም አስፈላጊው ማጣራት ተደርጐ ድህነቱ የተረጋገጠለትን ድሃ ከሳሽ በቂ መያዣ ወይም ዋስ ጥራ ማለቱ ስለድህነት ማስረጃው የተሰጠውን ውሣኔ እንደመቃረን ይቆጠራል፡፡ ስለሆነም በድሃ ደንብ መሠረት ክስ እንዲያቀርብ የተፈቀደለት ከሣሽ በቁጥር 200 መሠረት ለወጭና ኪሣራ ሲባል ዋስትና እንዲያቀርብ መያዣ እንዲያስይዝ መገደድ አይኖርበትም፡፡ አለበለዚያ በቁጥር 467 እና ተከታይ ድንጋጌዎችን

ዓላማ በመጣስ ፍትሕ የማግኘትን መብት እንደማጓደል ይቆጠራል የሚል ክርክር በአንድ በኩል ይቀርባል፡፡

በሌላ በኩል የድህነት ማስረጃው የአገልግሎት ወሰን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 473 እንደተመለከተው ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ወይም ማናቸውንም ለፍርድ ቤት መከፈል የሚገባውን ወጭ በሙሉ ወይም በከፊል ከመክፈል ነፃ የሚያደርግ እንጂ ከዚህ አልፎ የቀረበው ክስ ለሚያስከትለው ወጭና ኪሣራ አስቀድሞ ዋስትና እንዲያስይዝ ለማዘዝ የሚያስችሉ ሁኔታዎች በተገኙ ጊዜ ከዚሁ ግዴታው ነፃ የሚያደርግ ማስረጃ አይደለም፡፡ ዋናው መለየት ያለበት ጉዳይ ከክሱ አቀራረብ አንፃር ተመርምሮ በቁጥር 200 መሠረት ዋስትና እንዲያስይዝ የሚያበቁ ሁኔታዎች አሉ ወይስ የሉም የሚለው ነው፡፡ በእራሱ የክስ አቀራረብ ጉድለት ሳቢያ በሌላው ተከራካሪ ወገን ላይ አላስፈላጊ እንግልትና ኪሣራ ሊያደርስ አይገባውም፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ዓላማ ተከራካሪ ወገኖችን በእኩል ማየት እንደመሆኑ ያለአግባብ የተከሰሰው ተከሣሽ መብትም መጠበቅ ይኖርበታል፡፡ ፍትሕ የማግኘት መብትንም ሊሸርፍ አይችልም፡፡ በቂ ዋስትና እንዲያቀርብ የተገደደበትን ምክንያት አስወግዶ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 78/2//ለ/ መሠረት አስተካክሎ ማቅረብ ይችል ዘንድ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 201/1/ የተፈቀደ በመሆኑ በዚሁ መሠረት መፈፀም ስለሚችል፣ ወይም ደግሞ በቂ ዋስትና እንዲቀርብ የሚያስችል ሁኔታ ሳይኖር መያዣ ወይም ዋስ እንድጠራ መታዘዙ ተገቢ አይደለም በዚህም ምክንያት መዝገብ ተዘግቶብኛል የሚል ከሆነም በይግባኝ አቤቱታ አማካኝነት ማስተካከል የሚችልበት ማካካሻ ሥርዓት የተቀመጠ በመሆኑ ፍትህ የማግኘት መብትን የሚያጠብብ አይሆንም፡፡ በተለይም የዳኝነት ገንዘብ ክፍያ ክስን ያለአግባብ በእጅጉ እያጋነኑ እንዳያቀርቡ ለመገደብ የሚረዳ በመሆኑ ደሃ ስለተባለ ብቻ ያለክፍያ በዘፈቀደ ክስ የሚያቀርቡት ወገኖች መቆጣጠሪያ ሥርዓት መሆኑ መዘንጋት የለበትም የሚለው መከራከሪያ ይቀርባል፡፡

## ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ የሚሰጥ ውሣኔ እና ይግባኝ

አንድ ክርክር ተጀምሮ እስከሚያበቃ ድረስ የተወሰኑ የክርክር ደረጃዎችን ማለፉ አይቀሬ ነው፡፡ በዚህ በእያንዳንዱ የክርክር ደረጃ በየጊዜው ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ፣ ብይን ይሰጣል፡፡ በእያንዳንዱ ብይን እና ትዕዛዝ ላይ ቅር የተሰኘ ወገን ቅር በተሰኘ ቁጥር የይግባኝ አቤቱታ እንዲያቀርብ የሚፈቀድለት ከሆነ በአንድ ጉዳይ በተለያዩ ደረጃዎች በሚገኙ ፍ/ቤቶች እና በሥር ፍ/ቤት በርካታ መዝገቦች እንዲኖሩ /እንዲከፈቱ በር ይከፍታል፡፡ ይህም ክርክርን ሥርዓት አስይዞ መምራት የሚያስችል ካለመሆኑም በላይ ጊዜን፣ ጉልበትንና ገንዘብን ያለአግባብ የሚያባክን ይሆናል፡፡ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አስፈላጊነትም ይህንኑ አላስፈላጊ የሆኑትን ሙግቶች ለማስቀረት ነው፡፡

በዚህም መሠረት ጊዜያዊ አገልግሎት ባላቸው ትዕዛዞች ላይ ይግባኝ ማለት እንደማይቻል በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/3/ ተደንግጓል፡፡ ይህም ድንጋጌ ጊዜያዊ አገልግሎት ያላቸውን ትዕዛዝ ሲሰጥ ለአብነትም ያህል በማለት ካስቀመጣቸው ክርክሮች “. . . ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ፤” የሚለው ተጠቅሷል፡፡

ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ የሚሰጠው ዳኝነት ሁለት ዓይነት ነው፡፡ ይኸውም የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክስ ለማቅረብ የሚችል መሆኑን ወይም ጥያቄው ተቀባይነት ያለማግኘቱን የሚገልፅ ይሆናል፡፡ ድንጋጌውን ላይ ላዩን የተመለከትን እንደሆነ በጥያቄው ላይ የሚሰጠው ዳኝነት ምንም ይሁን ምን ዳኝነት ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ በሚሰጥ የዳኝነት ይግባኝ ማቅረብ እንደማይቻል ተደርጐ ሊወሰድ ይችላል፡፡

ይሁን እንጂ የዚሁ ድንጋጌ ይዞት ከላይ ከተጠቀሰው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ አስፈላጊነት አንፃር መታየት ይኖርበታል፡፡

የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱ በድሃ ደንብ ሥርዓት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል የሚባል ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ በዚህ ትዕዛዝ ላይ ቅር የተሰኘው ወገን /ተከሣሽ/ ቀሪውን ክርክር ይቀጥልና በመጨረሻ በሚሰጠው ውሣኔ የማይስማማ ከሆነ የይግባኝ አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ስለድሃ ደንብ ክስ አቀራረብ አስቀድሞ የተሰጠውን ትዕዛዝ እንደ አንድ የይግባኝ ምክንያት አድርጐ አጠቃሎ ማቅረብ እንዲችል እንጂ ክርክር ተሰምቶ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክሱ እንዲቀርብ በፈቀደው ትዕዛዝ ላይ ብቻ ይግባኝ እንዳይቀርብ ለመገደብ ተብሎ የተደነገገ ነው፡፡ ሆኖም የተሰጠው ትዕዛዝ ተገቢው የዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል በነፃ ለመክሰስ እንዲፈቀድ የቀረበው ጥያቄ ተቀባይነትን አላገኘም የሚል ከሆነ ከዚህ ትዕዛዝ በኋላ የሚቀጥል ክርክር አይኖርም፡፡ ከሣሹም ተገቢውን የዳኝነት ገንዘብ ካልከፈለ በቀር ክሱን ማቅረብ አይችልም፡፡ ይህ ዓይነቱ ዳኝነት ለተከሳሹ እንደመጨረሻ ፍርድ የሚቆጠር በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 320/1/ መሠረት ይግባኝ እንዲያቀርብ የተፈቀደ ነው፡፡ ስለሆነም በቁጥር 320/3/ መሠረት ስለድሃ ደንብ የክስ አቀራረብ ጥያቄን አስመልክቶ ትዕዛዝ የተሰጠ እንደሆነ በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ ይግባኝ ማቅረብ የሚቻል ስለመሆኑና አለመሆኑ በዚህ አኳኋን ሊታይ ይገባዋል፡፡

**(አባሪ ቁጥር 17)**

## <u>ዳኝነት ገንዘብ ሳይከፈል ክስ ያቀረበው ወገን በረታ ጊዜ ስለሚፈፀም ሥነ-ሥርዓት</u>

ዳኝነት ሳይከፈል ተከራክሮ የረታው ከሣሽ እንደ ፍርዱ ገንዘቡን በሚረከብበት ጊዜ ፍርድ አስፈፃሚው ሃብቱን ከማስረከቡ በፊት ለመንግስት መክፈል የሚገባውን ቀንሶ ገቢ ካደረገ በኋላ ቀሪውን ሃብት ማስረከብ አለበት በማለት በቁጥር 476 የተደነገገ በመሆኑ የዳኝነት ገንዘብ በቅድሚያ ረቺው በፍርድ ካገኘው ሃብት እንደሚከፈል በግልፅ ተመልክቷል፡፡ የዚህ ድንጋጌ የእንግሊዘኛ ግልባጭ ከዚህ የተለየ ቢሆንም ድንጋጌው ግልፅ መልዕክት የያዘ በመሆኑ ትርጉም አያስፈልገውም፡፡ ይኸውም የዳኝነት ገንዘብ ለመንግስት የሚከፈል ክፍያ በመሆኑ አስቀድሞ ለመሰብሰብ የታለመ ነው፡፡ ከዚህ ባሻገር የዳኝነት ገንዘብ ክሱ ያስከተለው ወጭ ነው፡፡ በክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭና ኪሣራ ማን ይክፈል የሚለውን ጉዳይ በሚሸፍነው በወጭና ኪሣራ ክፍል ታይቶ በመጨረሻ ወጭውን ማን ይሸፍን የሚለው ተለይቶ ትዕዛዝ የሚሰጥበት ጉዳይ ይሆናል፡፡

## (አባሪ ቁጥር 18)

## የወጭና ኪሣራ አወሳሰን

የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ ተፈጥሮ ሆኖ ክርክርን አይቶ ለመወሰን ጊዜ ይወስዳል፡፡ የዳኝነት ሥራ አካሄድን ቀልጣፋ ለማድረግ የፍ/ቤቶች አሠራር ማሻሻያ ኘሮግራም ያስገኘው ውጤት እንዳለ ሆኖ አሁንም ቢሆን የአንድ ጉዳይ ዕድሜ ርዝመት አጭር ነው የሚባል አይደለም፡፡ ጉዳይ በፍ/ቤት እጅ በቆየ ቁጥር ወጭና ኪሣራ ማስከተሉ የማይቀር ክስተት ነው፡፡ ስለሆነም አንድ ጉዳይ በውሣኔ ሳይቋጭ በቆየበት ጊዜ እና ጉዳዩን ለመከታተል ሲባል በሚወጣው ወጭና ኪሣራ መጠን መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለ ማለት ይቻላል፡፡

ፍ/ቤቶች ነፃና ገለልተኛ እንዲሁም ተጠያቂ ሊሆኑ ይገባል እንደሚባለው ሁሉ ተከራካሪ ወገኖችንም ተጠያቂ ማድረግ ከሚቻልበት ሥርዓት አንዱ ተገቢ እና ምክንያታዊ ባልሆነ ሙግት ሳቢያ ለተከሰተው ወጭና ኪሣራ ምክንያት የሆነውን ወገን ለይቶ እንዲክስ ማድረጊያው ሥርዓት ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይኸው ሥርዓት እጅግ አስፈላጊ መሆኑ እየታወቀ ብዙም ትኩረት የማይሰጥበት የሕግ ክፍል ስለመሆኑ ካለው የአሠራር ልምድ የሚስተዋል ነው፡፡

በመሆኑም ክርክር ተጠናቆ በቀረበልን ጉዳይ ላይ ውሣኔ በምንሰጥበት ጉዜ ክርክሩ ላስከተለው ወጭና ኪሣራ ኃላፊ መሆን የሚገባውን ወገንና ሊከፈል የሚገባውን የወጭና ኪሣራ ልክ በሚመለከት አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ውሣኔ በመስጠት ረገድ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

በወጭ እና ኪሣራ ጉዳይ ውሣኔ የሚሰጥበት በየትኛው መዝገብ ላይ እንደሆነ በቅድሚያ መመልከቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ማን መክፈል እንዳለበትና ስለኪሣራው መጠን አወሳሰን በዋናው ጉዳይ አስቀድሞ ዳኝነት ሊያርፍበት ይገባል፡፡ አልፎ አልፎ በዚሁ መሠረት ሳይከናወን ከተፈረደው ፍርድ ጋር ተዳብሎ የአፈፃፀም ክስ የሚቀርብበት ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ወጭና ኪሣራ በዋናው መዝገብ ሳይወሰን በቀጥታ በአፈፃፀም መዝገብ ቀርቦ ሊስተናገድ አይችልም፡፡ የአፈፃፀም ጉዳይ አስቀድሞ ውሣኔ ያረፈበትን ጉዳይ ማስፈፀም እንደመሆኑ የውጭና ኪሣራ ጉዳይም በቅድሚያ ታይቶ ፍርድ

ሊያርፍበት ይገባል፡፡ በፍርድ ውሣኔ ላይ ስለሚገለፁት ነገሮች በሚለው ርዕስ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 183/ሠ/ “ክሱን ለማስተካከል ወይም ይግባኙ ለማስፈፀም የተደረገውን ማናቸውንም የውጭ ዝርዝር፤ ወጭውን ማን እንደሚከፍልና የትኛው ንብረት ተሸጦ መክፈል እንደሚገባው መግለፅ፤ . . .” በሚል የተደነገገውም የወጭና ኪሣራ አወሳሰን የፍርዱ አካል መሆኑን የሚያስረዳ ነው፡፡

ከላይ የተመለከቱትን ነጥቦች ታሳቢ አድርጐ ወጭና ኪሣራውን በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕግ በ8ኛው መፅሐፍ ምዕራፍ አንድ ሥር ተደንግጓል፡፡

መሠረቱም በቁጥር 462 “ስለፍ/ቤቱ ሥልጣን” በሚል ርዕስ “በሌላ አኳኋን እንዲፈፀም በግልፅ ካልተደነገገ በቀር በክስ ምክንያት ስለሚከፈለው ስለማናቸውም ወጭና ኪሣራ፤ የሚከፍለውን ወገን፤ የወጭውንና የኪሣራውን ልክ የሚከፈልበትን የሃብት ምንጭ የአከፍፈሉን ሁኔታ ሌላውንና ተገቢ መስሎ የታየውን ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ፍ/ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ ሊሰጥ ይችላል፡፡” በሚል የተደነገገው ነው፡፡

ወጭና ኪሣራን ማን ይክፈል? ምን ያህል ይክፈል? የሚለውን አስመልክቶ በሌላ አኳኋን በግልፅ ተደንግጐ በተገኘ ጊዜ በዚሁ በቁጥር 462 በተመለከተው ድንጋጌ መሠረት ለፍ/ቤቱ የተሰጠው ሥልጣን /discretion/ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

ለአብነት ያህል ወጭና ኪሣራን ማን ይክፈል፤ ምን ያህል ይክፈል የሚለውን በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 278፣ 282፣ 285/2/፣ 476 እንዲሁም በፍ/ብ/ሕ/ቁ 1924 እና 1931፣ 162 በግልፅ ተለይቶ የተደነገገ በመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 መሠረት ለፍ/ቤቱ የተሰጠው ሥልጣን /discretionary power/ ተፈፃሚ ሊሆን አይችልም፡፡

ከዚህ ሁኔታ በቀር ወጭና ኪሣራን ማን መክፈል እንዳለበት፤ ምን ያህል እንደሚከፈል ፍ/ቤቱ ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ ተገቢ መስሎ የታየውን ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ተብሎ ሰፊ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡ “. . . ትክክል መስሎ በሚገምተው ሁኔታ. . .” የሚለው ሐረግ ከመጠቀሱ በቀር ምን ምን ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊወሰን እንደሚችል ጠቋሚ ሁኔታዎችን ሕጉ አላስቀመጠም፡፡ ሆኖም ይህንኑ ሥልጣን ከአጠቃላይ የወጭና ኪሣራ መርህ አንፃር ካየነው ስለወጭና ኪሣራ አወሣሰን የተቀመጡትን የተወሰኑ ቋሚ ደንቦች መሠረት

በማድረግ ሥራ ላይ የሚያውለው እንጂ እንዲሁ በዘፈቀደ ለመወሰን የሚያስችለው አለመሆኑን እንረዳለን፡፡

**“ማን ይክፈል”** የሚለውን በሚመለከት በመርህ ደረጃ ተረቺ ለረቺ ውጭና ኪሣራ እንዲከፍል የሚታዘዝ ሲሆን ከዚህ የተለየ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች፡ ያጋጠሙ እንደሆነ ግን ፍ/ቤቱ በዚህ ደንብ ላይመራ ይችላል፡፡ ከደንቡ የተለዩ ትዕዛዝ ለመሰጠት የሚያስችሉትን ሁኔታዎች ለመጥቀስ ያህል፡-

1. ከክርክር በፊትም ሆነ በክርክሩ ጊዜ በተከራካሪ ወገኖች የታየውን ባሕርይ /የቀን ልቦና መኖርና አለመኖር/ /conduct of the parties/
   - ቅን ልቦናን መሠረት ያደረገ ክርክርን አለመቅረብ
   - የሚከስበትን ጉዳይ አጋኖ ማቅረብ
   - በክርክር አቀራረብ ረገድ ግድፈት መፈፀም ወ.ዘ.ተ.
2. ከላይ የተመለከተው ጉድለት ያልታየ ከሆነ በክርክሩ በሙሉም ሆነ በከፊል የመረታቱን ሁኔታ /fact/
3. እንደተከሰሰ ይፈለግብኛል የሚለውን ዕዳ ተከሳሹ በፍ/ቤት እጁ ማስቀመጡንና ጉዳዩን ከክርክር በፊት በመጨረስ ረገድ ለፍ/ቤቱ አሳውቆ የተገኘ እንደሆነ የሚሉት ናቸው፡፡

በመሆኑም ምንም እንኳ አንዱ ወገን በአንድ ጉዳይ ላይ ረቺ መሆኑ ቢታወቅም ከላይ የተመለከቱት ሁኔታዎች መኖራቸው ከተረጋገጠ “ተረቺ ለረቺ ይክፈል /costs follow the event/” በሚለው መርህ ሳይመራ የተለየ ትዕዛዝ መስጠት ሥልጣኑ ነው፡፡

በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463/1/ “ተረቺው ለረቺው ኪሣራና ማናቸውንም ወጭ እንዲከፍል ፍ/ቤቱ ሲያዝ. . .” የሚለውም የሕጉ አነጋገር በማናቸውም ጉዳይ ፍ/ቤቱ ሁልጊዜ ተረቺ ለረቺ ወጭና ኪራሣ ይክፈል እያለ ይወስናል ማለት ሳይሆን ከግምት ውስጥ መግባት የሚገባቸውን ሁኔታዎች ካገናዘበ በኂላ ከዚህ ቋሚ መርህ የተለየ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችሉ ሁኔታዎች ባልተገኙ ጊዜ በጠቅላላ መርሁ መሠረት ተረቺ ለረቺ ይክፈል ከሚል መደምደሚያ የደረሰ እንደሆነ የሚሰጥ ትዕዛዝ መሆኑን አመላካች ነው፡፡

**{(አባሪ ቁጥር 19 (A)(B)(C)(D)(E)(F)}**

አንድ ክስ በድሃ ደንብ እንዲቀርብ ተፈቅዶ በክርክሩ ከሣሹ መርታቱ በታወቀ ጊዜ የዳኝነት ገንዘቡን ማን ይክፈል የሚለውን በሚመለከት በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 476 በተለየ ሁኔታ ረቺው ወይም ከሣሽ መክፈል እንዳለበት የሚያስገነዝብ ነው፡፡ የዳኝነት ገንዘብ ደግሞ ከወጭዎችና ኪሣራዎች አንዱ ነው፡፡ ይህንንም ድንጋጌ ከቁጥር 462 አንፃር ስናየው እርስ በእርሱ የተጋጨ ነው፡፡ ይኸው በቁጥር 462 በተመለከተው አጠቃላይ መርህ ከታዩ ከሳሽ ረቺ እንደመሆኑ መጠን ተረቺ ለረቺ ወጭና ኪሣራ ይክፈል ከሚለው መርህ የተለዩ ትዕዛዝ ለመስጠት የሚያስችል ምክንያት እስካልተገኘ ድረስ ይህንኑ የዳኝነት ገንዘብ ወጭ እራሱ እንደሸፈነ የሚቀርብት ምክንያት አይኖርም፡፡ እንዴት ማስታረቁ ይቻላል?

**(አባሪ ቁጥር 20)**

እስከአሁን ድረስ እንዳየነው ወጭና ኪሣራን ማን ይክፈል የሚለውን ነጥብ በሚመለከት በአንድ ክርክር አንድ ወገን በከፊልም ሆነ በሙሉ ስለረታ ብቻ ወጭና ኪሣራ የግድ ተረቺ በረቺ ይክፈል ማለት እንዳልሆነ ለመገንዘብ ችለናል፡፡ ተረቺ ለረቺ ሁልጊዜም ቢሆን ወጭና ኪሣራ እንዲከፍል የሚገደድበት ሥርዓት ከሌለ ውጤቱ ሁለቱም ወገኖች በየግላቸው ያወጡትን ወጭና ኪሣራ በየግላቸው ይቻሉ እንደማለት ነው፡፡ ስለሆነም ወጭና ኪሣራ ግራ ቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ የሚለው አሠራር ህጋዊ መሠረት ያለው መሆኑን እንረዳለን፡፡

## <u>ወጭና ኪሣራ ምን ያህል ይከፈል</u> (Taxation Costs)

ወጭና ኪሣራ ማለት በክርክር ጊዜ የወጣውን ወይም የባከነውን ገንዘብ፣ ጉልበት እና ጊዜ የሚመለከት ሲሆን በዝርዝር ካየነው የዳኝነት ገንዘብ፣ የጠበቃ ክፍያ፣ የክስ ማመልከቻም ሆነ የመከላከያ መልስ ለማዘጋጀት፣ ሰነዶችን ፎቶ ኮፒ በማድረግ የሚወጣውን ወጭ፣ ለምስክሮች አበልና መጓጓዣ ተብሎ የሚከፈለው ክፍያ ለመጥሪያ ለዕግድ ለቴምብር እና ለመሳሰሉት የሚወጣውን ወጭና እራሱ ተከራካሪው ወገን ያወጣውና ለወጣሁበት ለወረድኩበት ብሎ የሚያቀርበው ወጭ ሲሆን አወሳሰኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 ተመልክቷል፡፡ ወጭና ኪሣራውን ማን እንደሚከፍል ከተለየ በኋላ ምን ያህል ይክፈል በሚል መጠኑን ለመለየት በቁጥር 463 መሠረት መፈፀም እንደሚገባው አስገዳጅነት ባለው ሁኔታ ተደንግጓል፡፡ ይሁን እንጂ በአሠራር በልምድ

እንደሚታየው ዋናው ጉዳይ ሲወሰን ወጭና ኪሣራ በቁርጥ ይከፈል እየተባለ ልኩ ሲወሰን ይታያል፡፡ የቁርጥ አወሳሰን ለወጭና ኪሣራ ሲባል እንደገና ማሚገት አስፈላጊ አይደለም ከሚል መነሻ እንደሆነ ግምት መውሰድ የሚቻል ቢሆንም ይህ አሠራር ሕጋዊ መሠረት የሌለው ስለመሆኑ የሚያከራክር አይደለም፡፡

ይህ የቁርጥ አወሳሰን ሕጋዊ መሠረት የሌለው ከመሆኑም በላይ አሠራሩ በክርክር ምክንያት የወጣውን ወጭ በትክክል ለመለካት ስለማያስችል አንዱን ጠቅሞ ሌላውን ሊጐዳ ስለሚችል ቅሬታ ማስነሳቱ የማይቀር ነው፡፡ ቅሬታ በተነሣም ጊዜ መሠረቱ ስለኪሣራ ወጭ አወሳሰን ሕጉ ምን ይላል? የሚለው እንደመሆኑ በይግባኝ መሻሩ አይቀርም፡፡

**(አባሪ ቁጥር 21 ይመልከቱ)**

ስለሆነም በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ በሚሰጥበት ጊዜ ወጭና ኪሣራውን መክፈል የሚገባው ወገን ከተለዩ በኋላ ምን ያህል እንደሚከፈል ለማወቅ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 463 መሠረት የወጭውንና የኪሣራውን ልክ የሚያሳይ ዝርዝር ይቅረብ የሚል ትዕዛዝ በመስጠት መዝገቡ መዘጋት ይኖርበታል፡፡

የወጭው ዝርዝር በቀረበ ጊዜ መዝገቡ ከተዘጋ በኋላ እንደገና የቀረበው በውሣኔው መሠረት የወጭ ዝርዝር በመቅረቡ መሆኑን ቀጥሶ የዝርዝር ልኩን የሚያሳየው ማመልከቻ ከማስረጃዎች ጋር ለከፋዩ ወገን እንዲደርሰው ተደርጐ ስለወጭው አስፈላጊነትም ሆነ መጠን የበኩሉን ክርክር ከቀረበ በኋላ ፍ/ቤቱ በቁጥር 464 መሠረት መርምሮ ልኩን መወሰን አለበት፡፡

**(አባሪ ቁጥር 22)**

በቁጥር 464 መሠረት የወጭውን ልክ በመወሰን ረገድ ብዙውን ጊዜ ለክርክር ምክንያት የሚሆነው የጠበቃ አበል አወሳሰን ነው፡፡ የጠበቃ አበል ከወጭዎች አንዱ መሆኑ ታይቶ ይከፈል በተባለ ጊዜ በወጭ ዝርዝሩ ላይ የሚመለከተው በተከራካሪው ወገን እና በጠበቃው መካከል የተደረገው የዕውቀት ሥራ ውል ነው፡፡ በዚህ ውል መሠረት ለጠበቃ ክፍያ ፈፅሜያለሁና ይታይልኝ የሚል ክርክር ይቀርባል፡፡ የዚህ ውል የተፈፃሚነት ወሰን በተዋዋይ ወገኖች መካከል እንደሆነ ከፍ/ብ/ሕ/ቁ 1731 ም ሆነ

ከቁጥር 1952 መገንዘብ ይቻላል፡፡ በመሆኑም በሕግ ባለሙያ ታግዞ ለመከራከር ሲባል ምን ያህል ወጭ አስከትሏል የሚለውን በቁጥር 464 መሠረት ለመወሰን ይህ በጠበቃውና በተከራካሪው ወገን መካከል የተደረገው ውል የአሣሪነት ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡ ይልቁንም አስፈላጊነቱ ባያከራክርም እንኳ የክፍያው ወጭ ተገቢነት እንደማናቸውም ወጭ ታይቶ ከክርክሩ ውስብስብነት አንፃር ባለሙያው ሥራ ላይ ከዋለው ክህሎት፣ ልዩ ዕውቀትና ድካም፣ ክርክሩ ከፈጀው ጊዜ፣ ከጉዳዩ አስፈላጊነት፣ በጉዳዩ ከተካተተው የገንዘብ መጠን አንፃር እንደየሁኔታው በማየት የሚወሰን ነው፡፡ የጠበቃ አበል ምን ያህል ይከፈል የሚለውን በሚመለከት ሥልጣኑም በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 462 እንደተመለከተው ለፍ/ቤቱ የተሰጠ እንጂ ጠበቃውና ተከራካሪው ወገን ባደረጉት ውል ሊመራ እንደማይችል ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል፡፡

**(አባሪ ቁጥር 23)**